የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No.1
ADDIS ABABA 19th November, 2012


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፪፻፷፰/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፮ሺ፭፻፺፱
አባሪ ................................ ገጽ ፮ሺ፮፻፴፯


<u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፰/፪ሺ፭</u>

<u>ስለፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፳/፪ሺ፬ አንቀጽ ፳፯(፩) መሠረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፰/፪ሺ፭ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፳/፪ሺ፬ ነው፤


ያንዱ ዋጋ
Price 14.45


**<u>CONTENTS</u>**


Regulation No. 268/2012
Federal Police Officers Administration Council of Ministers Regulation .................. Page 6599
Annex ................................... Page 6637


**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 268/2012</u>**

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ADMINISTRATION OF FEDERAL POLICE OFFICERS</u>**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2010 and Article 27(1) of the Ethiopian Federal Police Commission Establishment Proclamation No. 720/2011.

**<u>PART ONE</u>**

**<u>GENERAL</u>**

1. **<u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Federal Police Officers Administration Council of Ministers Regulation No. 268/2012".

2. **<u>Definitions</u>**

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "Proclamation" means the Ethiopian Federal Police Commission Establishment Proclamation No. 720/2011;


ፖ.ሣ. ቁ.
P.O.Box 80001

ሸ) የማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፤
ቀ) ቢያንስ የአስረኛ ክፍል ትምህርቱን ያጠናቀቀ፤
በ) ለፖሊስነት የሚያበቃ አካላዊ ብቃትና የተሟላ ጤንነት ያለው፤
ተ) የወንጀል ሪከርድ የሌለበት፤
ቸ) የሚሰጠውን የመግቢያ ፈተና ያለፈ፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ቀ) የተደነገገው ቢኖርም የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ካለበትና ልዩ ድጋፍ ከሚሻ ክልል ወይም አርብቶ አደር ማኅበረሰብ ቢያንስ ፮ኛ ክፍልን ያጠናቀቀ ሰው ለፖሊስ አባልነት ሊመለመል ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖሊስ አባላት ምልመላ የሀገሪቱን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የፆታ ተዋፆን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ ለተለያዩ የፖሊስ ሙያ ሥራዎች የመመልመያ መስፈርቶችን በመመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፭. <u>መሠረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና</u>

፩/ ማንኛውም ምልምል ፖሊስ በፖሊስ አባልነት ከመቀጠሩ በፊት መሠረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና መውሰድና የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ አለበት፡፡

፪/ ኮሚሽኑ መሠረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና በመከታተል ላይ ለሚገኝ ማንኛውም ምልምል ፖሊስ፦
ሀ) ምግብ፣ መኝታ፣ የሥልጠና ዩኒፎርም፣ የጽህፈት መሣሪያ እና የኪስ ገንዘብ ይሰጠዋል፤
ለ) ለሚደርስበት ሕመም ወይም አደጋ አስፈላጊውን ህክምና እንዲያገኝ ያደርጋል፤
ሐ) ከሥልጠናው የተግባር ልምምድ ጋር ተያይዞ ለሚደርስበት የወንጀል ተጠያቂነት የራሱን የሕግ ባለሙያ በመመደብ ወይም ጠበቃ በመቅጠር ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

h) is not a member of any political organization;
i) has completed at least tenth grade;
j) has the physical fitness and health required to be a police officer;
k) has no criminal record;
l) passes the entrance exam;

may be recruited as police officer.

2/ Notwithstanding sub-article (1) (i) of this Article, a person who has completed at least 6th grade may be recruited from a region or pastoral community having shortage of educated persons and that deserves special support.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, recruitment of police officers shall take into account the representation of nations, nationalities, peoples and gender.

4/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Commission may issue directive on selection criteria for various police professions.

5. <u>**Basic Police Education and Training**</u>

1/ Every police recruit shall take basic police education and training and pass examination before being employed as a police officer.

2/ The Commission shall provide any police recruit participating in basic police education and training with:
a) food, lodging, training uniform, stationeries and pocket money;
b) necessary medical treatment in case of illness or accident;
c) free legal service through the assignment of its lawyer or the hiring of the service of an advocate in the case of any liability that may arise in connection with his practical training.

፪/ በከፍተኛ አመራር ደረጃ ላይ የሚገኝ የፖሊስ አባልን የመመደብ ወይም ከአንድ የኮሚሽኑ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ ሥራ ዘርፍ፣ ከክልል ፖሊስ ወደ ኮሚሽኑ ወይም ከኮሚሽኑ ወደ ክልል ፖሊስ፣ ከሌላ መንግሥታዊ መስሪያ ቤት ወደ ኮሚሽኑ ወይም ከኮሚሽኑ ወደ ሌላ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወይም ከኮሚሽኑ ወደ አህጉራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት የማዛወር ውሳኔ በኮሚሽነር ጀነራሉ ይሰጣል፡፡

፫/ በጀማሪ ወይም በመካከለኛ አመራር ደረጃ ላይ የሚገኝ የፖሊስ አባልን በአንድ የኮሚሽኑ ዘርፍ ውስጥ የሚደረግ ምደባ ወይም ዝውውር በዘርፉ ኃላፊ ይወሰናል፡፡

፬/ በጀማሪ ወይም በመካከለኛ አመራር ደረጃ ላይ የሚገኝ የፖሊስ አባልን የመመደብ ወይም ከአንድ የኮሚሽኑ የሥራ ዘርፍ ወደ ሌላ የሥራ ዘርፍ፣ ከክልል ፖሊስ ወደ ኮሚሽኑ ወይም ከኮሚሽኑ ወደ ክልል ፖሊስ ወይም ከሌላ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ወደ ኮሚሽኑ ወይም ከኮሚሽኑ ወደ ሌላ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት የማዛወር ውሳኔ በኮሚሽኑ የሰው ኃብት ልማት ዘርፍ ኃላፊ ይሰጣል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩)፣ (፫) እና (፬) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽነር ጀነራሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለዘርፍ ኃላፊዎች የተሰጠዉን የፖሊስ አባላት የመቅጠር፣ የመመደብና የማዛወር ስልጣን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር ወይም ይኸው ሥልጣን በማዕከል እንዲያዝ ለማድረግ ይችላል፡፡

፲. **<u>በዝውውር ወይም በተጠባባቂነት ስለመመደብ</u>**

፩/ ኮሚሽኑ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም የፖሊስ አባል ከአንድ የሥራ መደብ እኩል የሥራ ደረጃና ደመወዝ ወዳለው ሌላ ተመሳሳይ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሠራ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ ሁኔታዎች ሲያስገድዱ የአንድን ፖሊስ አባል ደመወዝ ሳይጨምር ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ በተጠባባቂነት መድቦ ማሠራት ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ላይ ወይም በተመደበበት የሥራ ቦታ ሊሠራ አለመቻሉ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፦

2/ The assignment of a police officer holding a senior management post or the transfer of such police officer from one sector of the Commission to another, from regional police to the Commission or vice versa, or from another government institution to the Commission or vice versa, or from the Commission to a continental or international organization shall be decided by the Commissioner General.

3/ The assignment or transfer of a police officer, holding a junior or middle level management post, within a sector of the Commission shall be decided by the head of the sector.

4/ The assignment of a police officer holding a junior or middle level management post or the transfer of such police officer from one sector of the Commission to another, from regional police to the Commission or vice versa, or from another government institution to the Commission or vice versa shall be decided by the head of the Commission's human resource sector.

5/ Notwithstanding the provision of sub-article (1), (3) and (4) of this Article, the Commissioner General may, where necessary, reduce or extend the power given to heads of sectors of the Commission to recruit, assign or transfer police officers or centralize such power.

10. **<u>Transfer or Acting Assignment</u>**

1/ The Commission, whenever necessary, may transfer any police officer to another similar position of an equal grade and salary or from one place of work to another place of work.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Commission may, in the case of compelling circumstances, assign a police officer to a position of higher grade in acting capacity for not more than six months without increment of salary.

3/ Where it is proved by a medical certificate that the nature of the work or the place of work a police officer assigned is not suitable because of his health problem:

ሀ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ወይም ቦታ ካለ በያዘው ደረጃ እንዲዛወር ይደረጋል፤ ወይም

ለ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ ቦታ ከሌለና አባሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ወደሚገኝ የሥራ ቦታ እንዲዛወር ይደረጋል፤ ሆኖም ዝቅ ብሎ በሚገኝ የሥራ ደረጃ ተመድቦ ለመስራት ፈቃደኛ ካልሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፬/ በአመራር ደረጃ ላይ ያለ የፖሊስ አባል በሥራ ገበታው ላይ በማይኖርበት ጊዜ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ከራሱ ቀጥሎ ወደታች በኃላፊነት ቀደምትነት ላለው ኃላፊ የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሠረት የሥልጣን ውክልና የሰጠ የፖሊስ አባል ወደሥራው ሳይመለስ ከሦስት ወር በላይ የሚቆይ ከሆነ የዘርፍ ኃላፊው ውክልናው እንዲራዘም በማድረግ የሥራ ደረጃው ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅማ ጥቅም ተወካዩ እንዲያገኝ ማድረግ ይችላል፡፡

፮/ የፖሊስ አባል የተመደበበት የሥራ መደብ የታጠፈ እንደሆነ በኮሚሽኑ ውስጥ ወደሚገኝ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው የሥራ መደብ እንዲዛወር ይደረጋል፤ ተመሳሳይ ደረጃ ያለው የሥራ መደብ የማይገኝ ከሆነም ደመወዙ ሳይቀነስ ዝቅ ያለ ደረጃ ወዳለው የሥራ መደብ እንዲዛወር ይደረጋል፤ ሆኖም ዝቅ ያለ ደረጃ ወዳለው የሥራ መደብ ለመዛወር ፈቃደኛ ካልሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

**፲፩. በመደበኛ ሥራ ላይ ወይም ውጪ ሆኖ ስለሚሰጥ ትምህርትና ሥልጠና**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለተመደበበት ሥራ ብቁ የሚያደርግ በመደበኛ ሥራ ላይ ወይም ውጪ ሆኖ የሚሰጥ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፪/ የፖሊስ አባሉ፡-

ሀ) በመደበኛ ሥራ ላይ ሆኖ የተከታተለው ትምህርት ወይም ሥልጠና የወሰደውን ጊዜ ያህል፤ ወይም

ለ) ከመደበኛ ሥራ ውጪ ሆኖ የተከታተለው ትምህርት ወይም ሥልጠና የወሰደውን ጊዜ እጥፍ፤

የማገልገል ግዴታ ይኖርበታል፡፡

a) he shall be transferred to another available vacant position or place of work with the same grade; or

b) shall be transferred to a lower grade where a vacant position of the same grade is not available and if he is willing; provided, however, that if he is not willing to be transferred to the lower grade, his service shall be terminated.

4/ Where a police officer holding a managerial post is absent from work, he may delegate a subordinate, who is next to him by seniority, for not more than three months.

5/ Where a police officer who has delegated a subordinate in accordance sub-article (4) of this Article absents himself for more than three months, the head of the sector may extend the delegation and allow the delegated police officer to get benefits resulting from the position.

6/ Where a position of a police officer is cancelled, he shall be transferred to a vacant position of similar grade available in the Commission or, where there is no vacant position of similar grade, he shall be transferred to a position of lower grade without reducing his salary; provided, however, that where he is not willing to be transferred to a position of lower grade, his service shall be terminated.

**11. On Job or Off Job Education and Training**

1/ Any police officer shall be given on job or o job education and training which qualifies h for the duty he is assigned for.

2/ The police officer shall be obliged to serve

a) for a period equivalent to the time he spent for attending on job educatio training; or

b) for a period equivalent to double th he has spent for attending o education or training.

## ክፍል ሦስት
## የማዕረግ እድገትና የኃላፊነት ቦታ ምደባ

**፲፪. ዓላማ**

የእድገት ወይም የኃላፊነት ቦታ ምደባ ዓላማ፡-

፩/ ኮሚሽኑ በየማዕረጉና የኃላፊነት ደረጃዉ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ፍላጎት ለሟሟላት፤ እና

፪/ የፖሊስ አባላትን በማበረታታት የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸም ለማሻሻል፤

ይሆናል፡፡

**፲፫. የማዕረግ እድገት**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል እድገትን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘዉ ሰንጠረዥ መሠረት የማዕረግ ቆይታ ጊዜ ሲያጠናቅቅ እና በሥራ አፈፃፀሙ አጥጋቢ ውጤት ሲያስመዘግብ የማዕረግ እድገት ያገኛል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከምክትል ሣጅን እስከ ዋና ሣጅን ድረስ ያሉት ማዕረጎች የሚሰጡት በውድድር ይሆናል፤

ለ) ከዋና ሣጅን ወደ ረዳት ኢንስፔክተር፣ ከኢንስፔክተር ወደ ዋና ኢንስፔክተር እና ከኮማንደር ወደ ረዳት ኮሚሽነር የሚደረጉ የማዕረግ እድገቶች የሚሰጡት በውድድር፣ በፈተና እና በሥልጠና ይሆናል፡፡

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የማዕረግ ዕድገት ማግኘት የሚችለው ከያዘው ማዕረግ ቀጥሎ ያለውን ማዕረግ ነው፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፫) ድንጋጌዎች ቢኖሩም፡-

ሀ) የላቀ ጀብዱ ወይም የስራ ውጤት ያስመዘገበ ወይም ልዩ የፈጠራ ሥራ የሠራ የፖሊስ አባል የተፋጠነ የማዕረግ እድገት ሊሰጠው ይችላል፤

ለ) የማወዳደሪያ መስፈርቱን የሚያሟላና የመምረጫ ፈተናውን የሚያልፍ በማንኛውም ዝቅ ያለ የማዕረግ ዕርከን ላይ የሚገኝ የፖሊስ አባል ለረዳት ኢንስፔክተርነት ማዕረግ መወዳደር ይችላል፡፡

፭/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከፖሊስ ሥራ ጋር ግንኙነት ባለው መስክ ዕውቅና ካለው የትምህርት ወይም ማሰልጠኛ ተቋም የተመረቀ መሆኑ የማዕረግ እድገት አያስጠውም፤ ሆኖም ለማዕረግ እድገት ውድድር የተወሰነ ነጥብ ሊያስጠው ይችላል፡፡

## PART THREE
## PROMOTION IN RANK AND ASSIGNMENT TO POSITION

**12. Objective**

The objective of promotion in rank or assignment to a position shall be:

1/ to staff the Commission with the necessary manpower at all ranks and positions; and

2/ to motivate police officers and thereby improve performance of the Commission.

**13. Promotion in Rank**

1/ Any police officer shall, unless subjected to prohibitive conditions, be eligible for rank promotion if the period of stay stipulated in the Annex hereto is completed and he has registered satisfactory performance.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, promotion shall be acquired through:

a) competition with respect to the ranks from Deputy Sergeant to Chief Sergeant;

b) competition, examination and training with respect to the ranks from Chief Sergeant to Assistant Inspector, from Inspector to Chief Inspector and from Commander to Assistant Commissioner.

3/ A police officer shall be promoted to a rank next to his present rank.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) and (3) of this Article:

a) any police officer who has registered outstanding achievement of heroism or performance or exceptional creativity may be entitled to accelerated promotion;

b) a police officer holding any lower rank may compete for the rank of Assistant Inspector if he meets the eligibility criteria and passes the selection exam.

5/ The fact that a police officer has graduated from an accredited educational or training institution in any field related to police service may not entitle him to rank promotion; provided, however, that certain points may be given to it when he competes for promotion.

፮/ የማዕረግ ዕድገት ማግኘት ማዕረጉ የሚያስገኘውን ጥቅማ ጥቅም ከሚያስጥ በስተቀር የኃላፊነት ቦታ ምደባን አያስጥም።

**፲፬. የኃላፊነት ቦታ ምደባ**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የኃላፊነት ቦታ ምደባን የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በኮሚሽኑ ውስጥ ለሚገኝ ክፍት የኃላፊነት ቦታ ለመወዳደር ይችላል።

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለኃላፊነት ቦታ መወዳደር የሚችለው ከያዘው ኃላፊነት ቦታ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ላለው የኃላፊነት ቦታ ብቻ ነው፤ ሆኖም የተለየ ሙያዊ ብቃት እንዳለው ሲረጋገጥና ለኮሚሽኑ የማኔጅመንት ኮሚቴ ቀርቦ ሲፈቀድ ከያዘው የኃላፊነት ቦታ በሁለት ደረጃ ከፍ ላለው የኃላፊነት ቦታ ሊወዳደር ይችላል።

፫/ ማንኛውም ተወዳዳሪ የኃላፊነት ቦታ ምደባ የሚሰጠው ለክፍት ቦታው ተፈላጊውን የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ አፈፃፀም ብቃት፣ መልካም ሥነ-ምግባር፣ የአገልግሎት ዘመን አሟልቶ ሲገኝና እንደአስፈላጊነቱ ለውድድሩ የተዘጋጀውን ፈተና ሲያልፍ ይሆናል።

፬/ የኃላፊነት ቦታ ምደባ ማግኘት ቦታው የሚያስገኘውን ደመወዝና ጥቅማጥቅም ከሚያስጥ በስተቀር የማዕረግ እድገት አያስጥም፤ ሆኖም ለማዕረግ ዕድገት ውድድር እንደ አንድ መስፈርት ግምት ውስጥ ይገባል።

**፲፭. ለእድገት ወይም ለኃላፊነት ቦታ ምደባ ቅድሚያ የሚያስጡ ሁኔታዎች**

፩/ ለማዕረግ እድገት ወይም ለኃላፊነት ቦታ ምደባ በእጩነት የቀረቡ የፖሊስ አባላት ተመሳሳይ የውድድር ውጤት ካስመዘገቡ የማዕረግ ቀደምትነት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል።

፪/ ለማዕረግ እድገት ወይም ለኃላፊነት ቦታ ምደባ በእጩነት የቀረቡ ተወዳዳሪዎች ተመሳሳይ ውጤት ካስመዘገቡና ተመሳሳይ የማዕረግ ቀደምትነት ደረጃ ላይ ከሆኑ ለእድገቱ ወይም ለምደባው የሚያልፈውን እጩ ለመለየት ልዩ ድጋፍ ከሚሹ ክልሎችና አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች ለመጡ የፖሊስ አባላት እና ለሴት ፖሊስ አባላት ቅድሚያ ይሰጣል።

6/ Promotion in rank may not entitle to assignment to a position, except to the benefits accorded to the rank.

**14. Assignment to a Position**

1/ Any police officer may, unless subjected to conditions prohibiting assignment to positions, compete for a vacant position available in the Commission.

2/ Any police officer may compete only for a position one step higher than the position he holds; provided, however, that he may be allowed to compete for a two steps higher position where it is authorized by the Management Committee of the Commission on the basis of his proven exceptional professional competence.

3/ Assignment to a position shall be granted if a candidate meets the educational qualification, performance level, ethical behavior and period of service required for the position and passes the examination offered as may be necessary.

4/ Assignment to a position may not entitle to promotion in rank, except to the salary and benefits accorded to the position; provided, however, that it shall be considered as one factor in competing for promotion in rank.

**15. Conditions Entitling Preference in Promotion or Assignment to a Position**

1/ Where police officers compete as candidates for promotion in rank or assignment to a position score equal results, preference shall be given on the basis of seniority.

2/ Where candidates for promotion in rank or assignment to a position score equal results and have the same level of seniority, preference shall be given to police officers from regions and pastoral communities entitled to affirmative support and to female police officers to select the final candidate.

፲፮. <u>እድገትና የኃላፊነት ቦታ ምደባ የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች</u>

ማንኛውም የፖሊስ አባል፦

፩/ አገልግሎቱ በዚህ ደንብ መሠረት የሚራዘምለት ካልሆነ በስተቀር ጡረታ ለመውጣት አንድ ዓመት ወይም ከዚያ በታች የቀረው ከሆነ፤

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት የዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበትና የሪከርድ ጊዜዉ ያላበቃ ከሆነ፤ ወይም

፫/ በወንጀል ድርጊት ተከሶ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተቀጣ ከሆነና ቅጣቱን ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ሁለት ዓመት ያልሞላው ከሆነ፤

ለማዕረግ እድገት ወይም ለኃላፊነት ቦታዎች ምደባ መወዳደር አይችልም።

፲፯. <u>እድገትንና የኃላፊነት ቦታ ምደባን ስለመሠረዝ</u>

የሀሰት ማስረጃ በማቅረብ የተገኘ ወይም ህግን በመተላለፍ የተሰጠ የማዕረግ እድገት ወይም የኃላፊነት ቦታ ምደባ በዲስፕሊንና በወንጀል የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም ጊዜ ይሠረዛል።

፲፰. <u>የማዕረግ እድገትን የማጽደቅና የመሠረዝ ሥልጣን</u>

፩/ ከረዳት ኮሚሽነር እስከ ኮሚሽነር ደረጃ ድረስ ያለው የማዕረግ እድገት በኮሚሽነር ጀነራሉ አቅራቢነት በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ይጸድቃል።

፪/ ከረዳት ሣጅን እስከ ኮማንደር ደረጃ ድረስ ያለው የማዕረግ እድገት በኮሚሽነር ጀነራሉ ይጸድቃል።

፫/ ማንኛውንም እድገት የመሠረዝ ውሳኔ የሚሰጠው የዚህ ዓይነቱን እድገት ለማጽደቅ ሥልጣን ያለው አካል ይሆናል።

፬/ ኮሚሽነር ጀነራሉ በዚህ አንቀጽ መሠረት እድገት የማጽደቅና የመሠረዝ ሥልጣኑን እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላለፍ ይችላል።

፲፱. <u>የማዕረግ ምልክት</u>

ማንኛውም የፖሊስ አባል ፖሊስነቱንና ማዕረጉን ሊያሳይ የሚችል የማዕረግ ምልክት ከደንብ ልብሱ ጋር ያደርጋል።

፳. <u>ስለእድገት ኮሚቴ</u>

ኮሚሽኑ ለማዕረግ እድገትና ለኃላፊነት ቦታ ምደባ እጩዎችን አወዳድሮ በመምረጥ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የእድገት ኮሚቴ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአንድ በላይ የእድገት ኮሚቴዎችን በመመሪያ ሊያቋቁም ይችላል።

16. **<u>Conditions Prohibiting Promotion and Assignment to Positions</u>**

A police officer may not be eligible to compete for promotion in rank or assignment to positions where:

1/ he has one or less than one year to retire unless his service is extended in accordance with this Regulation;

2/ he was subjected to a disciplinary penalty in accordance with this Regulation and the record period has not barred by limitation; or

3/ he was convicted and sentenced by a competent court of law for commission of a crime, and two years have not lapsed after completion of the penalty.

17. **<u>Revocation of Promotion and Assignment to a Position</u>**

A promotion in rank or an assignment to a position obtained on the basis of fraudulent evidence or granted in contravention of the law shall, without prejudice to disciplinary and criminal liability, be revoked at any time.

18. **<u>Power to Approve and Revoke Promotion in Rank</u>**

1/ A promotion in rank from Assistant Commissioner up to Commissioner shall be approved by the Minister of Federal Affairs upon the recommendation of the Commissioner General.

2/ A promotion in rank from Assistant Sergeant up to Commander shall be approved by the Commissioner General.

3/ Revocation of any promotion shall be decided by the body having the power to approve such promotion.

4/ The Commissioner General may, as necessary, delegate his powers to approve and revoke promotions under this Article to other officials of the Commission.

19. **<u>Rank Insignia</u>**

Each police officer shall wear a rank insignia with his uniform indicating his being a police officer and the level of his rank.

20. **<u>Promotion Committee</u>**

The Commission may, by directive, establish a promotion committee or where necessary more than one committees to select and recommend candidates for promotions in ranks and assignments to positions.

## ክፍል አራት
## ስለደመወዝ፣ የደንብ ልብስ፣ ትጥቅ፣ አርማና መታወቂያ

**፳፩. ስለደመወዝ ስኬል**

፩/ ኮሚሽኑ ለፖሊስ አባላት የሚያገለግል የደመወዝ ስኬል አጥንቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል በመንግስት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በየጊዜው በሀገሪቱ የሚከሰቱ የኢኮኖሚ ለውጦችንና ሌሎች ሁኔታዎችን እያገናዘበ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ጥናት እያካሄደ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግስት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፫/ የደመወዝ ስኬሉ ለእያንዳንዱ የሥራ ደረጃ መነሻና መድረሻ ደመወዝ እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል፡፡

**፳፪. ስለደመወዝ ክፍያ አፈፃፀም**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ደመወዙ በየወሩ መጨረሻ ይከፈለዋል፡፡

፪/ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ደመወዝ በሥራ ቀንና በሥራ ቦታ የሚከፈል ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የደመወዝ ክፍያ ኮሚሽኑ በሚመርጠው ባንክ አማካይነት ሊፈፀም ይችላል፡፡

፬/ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ካልሆነ በስተቀር ደመወዝ የሚከፈለው ለፖሊስ አባሉ ለራሱ ወይም የፖሊስ አባሉ ለወከለው ሰው ብቻ ነው፡፡

**፳፫. ስለደመወዝ ጭማሪ**

፩/ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱ አጥጋቢ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የፖሊስ አባል በያዘው ማዕረግ በየሁለት ዓመቱ የደመወዝ ጭማሪ ያገኛል፡፡

፪/ የፖሊስ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያገኘው የደመወዝ ጭማሪ በኮሚሽኑ መመሪያ በሚወሰነው መሠረት እንደ ሥራ አፈፃፀም ውጤቱ መጠን የተለያየ የእርከን ጭማሪ ይሆናል፡፡

፫/ አጥጋቢ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ያላገኘ የፖሊስ አባል የደመወዝ ጭማሪ አያገኝም፡፡

፬/ የማዕረግ እድገት ያገኘ የፖሊስ አባል ለአዲሱ ማዕረግ የተወሰነውን መነሻ ደመወዝ ያገኛል፣ እድገቱን ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ ለአዲሱ ማዕረግ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ የአንድ እርከን ደመወዝ ጭማሪ ያገኛል፡፡

## PART FOUR
## SALARY, UNIFORM, EQUIPMENT, EMBLEM AND IDENTITY CARD

**21. Salary Scale**

1/ The Commission shall study and submit to the Ministry salary scale applicable to police officers and implement same upon approval by the government.

2/ The Commission shall, where necessary, review the salary scale and submit to the Ministry by taking into account economic changes and other factors taking place in the country and implement same upon approval by the government.

3/ The salary scale shall consist of the base and ceiling salaries for each job position, as well as steps which indicate periodical salary increments.

**22. Payment of Salary**

1/ Any police officer shall be paid his salary at the end of every month.

2/ Unless the situation dictates otherwise, salary shall be paid on working day and at the place of work.

3/ Notwithstanding sub-article (2) of this Article, payment of salary may be effected through a bank selected by the Commission.

4/ Unless ordered by a court of law, salary shall be paid to a police officer in person or to a person delegated by him.

**23. Salary Increment**

1/ A police officer whose performance evaluation result is satisfactory or above shall be entitled to salary increment every two years in his present rank.

2/ The salary step increment to be given to a police officer pursuant to sub-article (1) of this Article shall vary depending on the result of his performance evaluation as determined by directive of the Commission.

3/ A police officer whose performance evaluation result is unsatisfactory may not be entitled to salary increment.

4/ A police officer promoted in rank shall be entitled to get the base salary of the new rank; provided, however, that where the existing salary exceeds or is equal to the base salary of his new rank, he shall be entitled to get a one step salary increment.

፭/ አንድ አባል ከፍ ያለ የኃላፊነት ቦታ ምደባ ሲሰጠው ለአዲሱ ቦታ የተመደበውን መነሻ ደመወዝ ያገኛል፤ ሆኖም ምደባውን ከማግኘቱ በፊት ያገኝ የነበረው ደመወዝ ለአዲሱ ቦታ ከተወሰነው መነሻ ደመወዝ በላይ ወይም እኩል የሆነ እንደሆነ የአንድ እርከን ደመወዝ ጭማሪ ያገኛል፡፡

## ፳፬. ደመወዝን ስለመያዝና ስለመቁረጥ

፩/ የማንኛውም የፖሊስ አባል ደመወዝ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሰረት ካልሆነ ወይም የፖሊስ አባሉ በጽሁፍ ካልተስማማ በስተቀር በዕዳ ሊያዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቻቻል አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከማንኛውም የፖሊስ አባል የወር ደመወዝ ላይ ሊቆረጥ የሚችለው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ካልተጣራ ደመወዙ አንድ ሦስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

## ፳፭. ስለአበልና ጥቅማ ጥቅም

፩/ ኮሚሽኑ የቀለብ፣ የአበልና የሌሎች ጥቅማ ጥቅም ክፍያዎችን ዓይነትና መጠን በማጥናት ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ በመንግስት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፪/ ማንኛውም አበል ወይም ጥቅማጥቅም ለፖሊስ አባላት የሚሰጠው የኮሚሽኑን ሥራ በብቃት ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

፫/ በእኩል የማዕረግና የኃላፊነት ደረጃ ላይ የሚገኙ የፖሊስ አባላት እኩል አበልና ጥቅማጥቅም ያገኛሉ፡፡

## ፳፮. የደንብ ልብስና ትጥቅ

፩/ የፖሊስ አባላት ለሥራና ለክብረ በዓል አስፈላጊ የሆኑ የደንብ ልብሶች እና ትጥቆች ይሰጧቸዋል፡፡

፪/ የሥራና የክብረ በዓል ደንብ ልብሶች ቀለማት እንዲሁም በየደረጃዉ ለሚገኙ የፖሊስ አባላት ሊሰጡ የሚገባቸው የደንብ ልብሶችና ትጥቆች ዓይነቶች ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

## ፳፯. ዓርማና ባጅ

፩/ ኮሚሽኑ ለሕግ ተገዥነትን፣ ሕግ አስከባሪነትንና የሕዝብ አገልጋይነትን የሚያንፀባርቅ ዓርማ ይኖረዋል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ ዓርማ በፖሊስ መታወቂያ ካርድ፣ በመለዮ፣ በደንብ ልብስ፣ በተሽከርካሪዎችና ኮሚሽኑ በሚወስናቸው ሌሎች ቦታዎች አገልግሎት ላይ ሊውል ይችላል፡፡

፫/ የኮሚሽኑ የሥራ ክፍሎች እንደሥራ ባህሪያቸው ከኮሚሽኑ ዓርማ በተጨማሪ የየራሳቸው መለያ ዓርማ ሊኖራቸው ይችላል፡፡

5/ A police officer assigned to a higher position shall be entitled to get the base salary of the new position; provided, however, that where the existing salary exceeds or is equal to the base salary of his new position, he shall be entitled to get a one step salary increment.

## 24. Attachment and Deduction of Salary

1/ The salary of a police officer may not be attached, deducted or set off except in accordance with the law, the order of a court or the written agreement of the police officer.

2/ The total amount of money that may be deducted from the monthly salary of a police officer pursuant to sub-article (1) of this Article may not exceed one-third of his gross salary.

## 25. Allowances and Benefits

1/ The Commission shall conduct and submit to the Ministry studies on the types and amounts of ration, allowances and other benefits and implement same upon approval by the government.

2/ Any allowance or benefit may be given to police officers if it is necessary to effectively carry out the functions of the Commission.

3/ Police officers having the same rank and level of responsibility shall receive the same amount of allowance and benefit.

## 26. Uniform and Equipment

1/ Police officers shall be provided with the necessary uniforms, for duty and ceremony, and equipment.

2/ The colors of uniforms for duty and ceremony as well as the kinds of uniforms and equipment to be issued to police officers at every level of ranks shall be determined by directive to be issued by the Commission.

## 27. Emblem and Badge

1/ The Commission shall have emblem signifying respect for law, enforcing law and serving the people.

2/ The emblem of the Commission may be used on police officers' identity cards, caps, uniforms, police vehicles, and on any other place determined by the Commission.

3/ Sectors of the Commission may, in addition to the emblem of the Commission, have their own emblems depending on the nature of the services they provide.

፬/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የሥራ ድርሻውን የሚገልፅ ባጅ ይኖረዋል፡፡

፭/ የአርማና የባጅ ቀለም፣ ዓይነትና አጠቃቀም ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፰. የመለያ ቁጥርና መታወቂያ ካርድ**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በኮሚሽኑ የሚሰጥ መለያ ቁጥርና መታወቂያ ካርድ ይኖረዋል፡፡

፪/ የፖሊስ አባል መለያ ቁጥር በሚለብሰው የደንብ ልብስ ላይ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ በግራ በኩል ደረቱ ላይ ይደረጋል፡፡

፫/ የፖሊስ አባል መታወቂያ ካርድ የኮሚሽኑን ዓርማ፣ የፖሊስ አባሉን ፎቶግራፍ፣ ሙሉ ስሙን፣ የሥራ ክፍሉን፣ የሥራ ደረጃዉን፣ ማዕረጉን፣ የደሙን ዓይነት እና መለያ ቁጥሩን መያዝ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ሕግን ሲያስከብር የመታወቂያ ካርዱን ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አምስት
## የሥራ ሰዓትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች

**፳፱. መደበኛ የሥራ ሰዓት**

፩/ የኮሚሽኑ የፖሊስ አገልግሎት በቀን ፳፬ ሰዓት እና በሳምንት ፯ ቀናት የሕዝብ በዓል ቀናትን ጨምሮ ያለማቋረጥ ይሰጣል፡፡

፪/ የማንኛውም ፖሊስ አባል መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን ስምንት ሰዓት ይሆናል፤ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ትርፍ ሰዓት እንዲሠራ ሊታዘዝ ይችላል፡፡

፫/ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሰራ የፖሊስ አባል የማካካሻ እረፍት ይሰጠዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ ለተወሰኑ ሥራዎች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስለሚፈፀምበት ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

**፴. የዓመት እረፍት ፈቃድ መርሆዎች**

፩/ የዓመት እረፍት ፈቃድ የሚሰጠዉ የፖሊስ አባሉ ለተወሰነ ጊዜ በማረፍ አገልግሎቱን በታደሰ መንፈስ እንዲቀጥል ለማስቻል ነዉ፡፡

፪/ ማንኛውም አዲስ የተቀጠረ የፖሊስ አባል ፲፩ ወር አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት የዓመት እረፍት ፈቃድ የማግኘት መብት አይኖረውም፡፡

፫/ የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ አይለወጥም፡፡

4/ Each police officer shall be issued with a badge which describe his role.

5/ The colors, type and use of emblem and badge shall be determined by directive to be issued by the Commission.

**28. Identification Number and Identity Card**

1/ Any police officer shall have an identification number and an identity card issued by the Commission.

2/ The identification number of a police officer shall be affixed conspicuously on the upper front left side of his uniform.

3/ The identity card of a police officer shall contain the emblem of the Commission and the photograph, full name, department, responsibility, rank, blood type and the identification number of the police officer.

4/ Any police officer shall show his identity card while enforcing the law.

## PART FIVE
## WORKING HOURS AND VARIOUS LEAVES

**29. Regular Working Hours**

1/ The police service of the Commission shall be delivered 24 hours a day and seven days in a week, including holidays, without interruption.

2/ The regular working hours of a police officer shall be eight hours a day; provided, however, that when situation compels, he may be ordered to work over-time.

3/ A police officer who has worked over-time shall be granted compensatory time off.

4/ Notwithstanding sub-article (3) of this Article, the Commission may issue directive on payment of over-time for certain duties.

**30. Principles of Annual Leave**

1/ The purpose of annual leave is to enable a police officer to get rest and resume service with renewed strength.

2/ A fresh recruit may not be entitled to annual leave before serving for 11 months.

3/ There may be no payment in lieu of annual leave.

**፴፩. የዓመት እረፍት ቀናት**

፩/ አንድ ዓመት ያገለገለ የፖሊስ አባል ፳ የሥራ ቀናት የዓመት እረፍት ፈቃድ የመዉሰድ መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ የፖሊስ አባል ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት እረፍት ፈቃድ ይሰጠዋል፤ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ ዓመት እረፍት ፈቃድ ከሠላሳ የሥራ ቀናት መብለጥ አይችልም፡፡

፫/ የፖሊስ አባሉ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል የሰጠው አገልግሎት ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የሚታሰብ ይሆናል፡፡

**፴፪. የዓመት እረፍት ፈቃድ አሰጣጥ**

፩/ የዓመት እረፍት ፈቃድ የኮሚሽኑን የሰዉ ኃይል ስምሪት መሠረት በማድረግና በተቻለ መጠን የአባሉን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጅ ዓመታዊ መርሀ ግብር መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ይሰጣል፡፡

፪/ አንድ የፖሊስ አባል የዓመት እረፍት ፈቃድ በሚወስድበት ጊዜ በእረፍት ላይ የሚቆይበትን የአንድ ወር ደመወዙን በቅድሚያ ሊወስድ ይችላል፡፡

፫/ የፖሊስ አባል ሲጠይቅና የቅርብ አለቃው ሲስማማ የዓመት እረፍት ፈቃድ ተከፋፍሎ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የዓመት እረፍት ፈቃድ የወሰደና የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት አገልግሎቱን በገዛ ፍቃዱ ያቋረጠ የፖሊስ አባል አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ በፈቃድ ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

**፴፫. የዓመት እረፍት ፈቃድን ስለማስተላለፍ**

፩/ የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ለፖሊስ አባል የዓመት እረፍት ፈቃድ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰጠው ያልተቻለ እንደሆነ በቅርብ አለቃው እስከ ሁለት የበጀት ዓመታት እንዲተላለፍ ሊደረግ ይችላል፤ ሆኖም የተጠራቀመው የዓመት እረፍት ፈቃድ በሦስተኛው በጀት ዓመት መሰጠት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ኮሚሽነር ጀነራሉ ሁኔታው እስከሚስተካከል ድረስ የዓመት እረፍት ፈቃድ እንዳይሰጥ ሊያግድ ይችላል፡፡

፫/ የሥራው ሁኔታ በማስገደዱ ምክንያት በፈቃድ ላይ ያለ የፖሊስ አባል ፈቃዱን አቋርጦ እንዲመለስ ማድረግና ያልተጠቀመዉን ቀሪ የዓመት እረፍት ፈቃዱን ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት የዓመት እረፍት ፈቃዱን አቋርጦ ወደ ሥራ የሚመለስ የፖሊስ አባል የመጓጓዣና የውሎ አበል ይከፈለዋል፡፡

**31. Duration of Annual Leave**

1/ A police officer who has served for one year shall be entitled to 20 working days of annual leave.

2/ A police officer who has served for more than one year shall be entitled to one working day additional leave for each year of service; provided, however, that the total number of days of annual leave may not exceed thirty working days.

3/ A service rendered in another government office shall be considered for computation of leave in accordance with this Article.

**32. Manner of Granting Annual Leave**

1/ Annual leave shall be granted within the budget year in accordance with a schedule prepared on the basis of the human resource deployment plan of the Commission and, in as much as possible, by taking into account the preference of the police officer.

2/ A police officer shall be entitled to advance payment of his monthly salary at the time of taking his annual leave.

3/ Annual leave may be granted on a piece meal basis if the police officer requests and his immediate supervisor agrees.

4/ A police officer who has taken annual leave in accordance with sub-article (1) of this Article and who has resigned before the end of the budget year shall be liable to pay back the salary received while on leave in proportion to the period not served.

**33. Postponement of Annual Leave**

1/ Where it is not possible to grant annual leave within the same budget year due to compelling circumstances, the immediate supervisor of a police officer may postpone the annual leave for up to two budget years; provided, however, that the accumulated annual leave shall be granted to the police officer within the third budget year.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Commissioner General may, in exceptional circumstances, suspend the granting of annual leave until the situation is normalized.

3/ A police officer who is on annual leave may be re-called to duty and his unused leave be postponed if the situation compels to do so.

4/ A police officer who is re-called to duty pursuant to sub-article (3) of this Article shall be paid for his transport expenses and per-diem.

**፴፬. ስላልተወሰደ የዓመት እረፍት ፈቃድ**

፩/ የዚህ ደንብ አንቀፅ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም የፖሊስ አባሉ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት ያልተወሰደ የዓመት እረፍት ፈቃድ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተላልፎ የነበረ የዓመት እረፍት ፈቃድ በሦስተኛው የበጀት ዓመት ሊሰጥ ካልተቻለ የስራ ቀናቶች ብቻ ታስበው በገንዘብ እንዲለወጥ ይደረጋል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ወደ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ለተዛወረ የፖሊስ አባል ተፈፃሚ አይሆንም፤ ሆኖም ያልተወሰ ደው የዓመት እረፍት ፈቃድ ወደ ተዛወረበት የመንግስት መስሪያ ቤት ይተላለፍለታል፡፡

**፭. የወሊድ ፈቃድ**

፩/ ነፍሰጡር የሆነች የፖሊስ አባል፦

ሀ) ሐኪም በሚያዘው መሠረት ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ፤ ወይም

ለ) ከመውለዷ በፊት እረፍት እንድታደርግ በሐኪም ስትታዘዝ፤

ደመወዝ የሚከፈልበት እረፍት ይሰጣታል፡፡

፪/ የፖሊስ አባሏ መውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት ፴ ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ እና ከወለደችበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ፷ ተከታታይ ቀናት ደመወዝ የሚከፈልበት የወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የፖሊስ አባሏ የተሰጣት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከማለቁ በፊት ከወለደች ያልተጠቀመችበትን ቀሪ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከወለደች በኋላ እንድትጠቀም ይደረጋል፡፡

፬/ የፖሊስ አባሏ የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባሉት የሥራ ቀናት የምትቆይበት እረፍት በበጀት ዓመቱ ባላት የዓመት እረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የዓመት እረፍት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ በሚቀጥለው የበጀት ዓመት የእረፍት ፈቃዷ ይተካል፡፡

፭/ የፖሊስ አባሏ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተወሰነዉን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመምና ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋት መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፴፮ በተደነገገዉ መሠረት የሕመም ፈቃድ መዉሰድ ትችላለች፡፡

፮/ የፖሊስ አባል የትዳር ጓደኛው ስትወልድ ቤተሰቡንና ባለቤቱን ለመንከባከብ ደመወዝ የሚከፈልበት አምስት የሥራ ቀናት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

**34. Unused Annual Leave**

1/ Notwithstanding the provision of sub-article (3) of Article 30 of this Regulation, payment shall, on the basis of calculating only the working days, be effected in lieu of unused annual leave due to termination of service or annual leave postponed in accordance with sub-article (1) of Article 33 of this Regulation and that cannot to be granted in the third budget year.

2/ Sub-article (1) of this Article may not apply to a police officer who is transferred to another government office; provided, however, that the unused annual leave shall be transferred to the said government office.

**35. Maternity Leave**

1/ A pregnant police officer shall be entitled to paid leave:

a) for medical examination in relation to her pregnancy as recommended by a physician; or

b) for rest before delivery if recommended by a physician.

2/ A pregnant police officer shall be entitled to a period of 30 consecutive days of prenatal leave with pay preceding the presumed date of her confinement and a period of 60 consecutive days of maternity leave after her confinement.

3/ If the pregnant police officer delivers before the completion of prenatal leave which is granted in accordance with sub-article (2) of this Article, the unused prenatal leave will be granted after her confinement.

4/ If the pregnant police officer does not deliver on the presumed date, the leave days subsequently taken before her confinement shall be replaced by the annual leave she is entitled to within the budget year or that of the following budget year if no annual leave is left within the budget year.

5/ The police officer shall be entitled, where recommended by a physician, to sick leave in accordance with Article 36 of this Regulation if she becomes sick after completion of her maternity leave provided under sub-article (2) of this Article.

6/ A police officer shall be entitled to a paternity leave with pay for five working days at the time of the delivery of his wife.

## ፴፮. የሕመም ፈቃድ

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በሕመም ምክንያት ሥራ መሥራት ያልቻለ እንደሆነ በሐኪም ማስረጃ ሲደገፍ የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለፖሊስ አባሉ የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወሰድም ሕመሙ ከጀመረበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው ፲፪ ወር ውስጥ ከስምንት ወር ወይም በአራት ዓመት ውስጥ ከ፲፪ ወር መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር እና ለሚቀጥሉት ሁለት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር ይሆናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የጊዜ ገደብ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸዉ ዉስጥ ባለባቸዉ የፖሊስ አባላት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፭/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ሲታመም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለቅርብ አለቃው ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፴፯. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ፈቃድ

፩/ ከሥራ የመጣ ጉዳት የደረሰበት የፖሊስ አባል ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስኪመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታው መሥራት ያልቻለ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የጉዳት ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

፪/ በጉዳት ፈቃድ ላይ ያለ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) ለህክምና ምርመራ ለመቅረብ እምቢተኛ ከሆነ ወይም ቸል ያለ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ሆን ብሎ ምርመራውን ያደናቀፈ ወይም ያለበቂ ምክንያት ያጓተተ እንደሆነ፤

ለ) ከጉዳት የሚድንበትን ጊዜ ለማዘግየት በማሰብ ህክምናውን በተገቢው መንገድ ያልተከታተለ እንደሆነ፤ ወይም

ሐ) በኮሚሽኑ የወጣውን የህክምና መመሪያ የተላለፈ እንደሆነ፤

በፈቃድ ላይ ሆኖ የሚያገኘው ክፍያ ይታገዳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ለክፍያ መታገድ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎች እንደተወገዱ የሚደረገው ክፍያ እንደገና ይቀጥላል፤ ሆኖም እገዳው ፀንቶ ለቆየበት ጊዜ ያልተከፈለውን ክፍያ የመክፈል መብት አይኖርም፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ለምልምል የፖሊስ ሠልጣኝም ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 36. Sick Leave

1/ Any police officer shall be entitled to sick leave, when recommended by a physician, where he is unable to work due to sickness.

2/ The duration of sick leave to be granted to a police officer in accordance with sub-article (1) of this Article may not exceed eight month with in twelve month or twelve month with in four years, whether counted consecutively or intermittently starting from the first day of sickness.

3/ Sick leave to be granted in accordance with sub-article (2) of this Article shall be with full pay for the first six months and with half pay for the next two months.

4/ The time limit provided under sub-article (2) of this Article may not apply to HIV/AIDS positive police officers.

5/ Where a police officer is absent from duty due to sickness, he shall, as soon as possible, notify to his immediate supervisor unless prevented by force majeure.

## 37. Leave Due to Employment Injury

1/ A police officer who has sustained an employment injury shall be entitled to injury leave with pay until he recovers to resume work or until it is medically certified that he is permanently disabled.

2/ A police officer, who is on injury leave, may be suspended from receiving payment where he:

(a) refuses or neglects to submit himself to medical examination or in any way intentionally obstructs or unnecessarily delays such examination;

(b) does not follow-up his medical treatment properly to intentionally retard his recovery; or

(c) violates the medical directive issued by the Commission.

3/ As soon as the circumstances that occasioned the suspension pursuant to sub-article (2) of this Article ceases, the payment shall recommence; provided, however, that there may be no entitlement to back-pay for the period of suspension.

4/ The provisions of this Article shall also be applicable to a recruit police trainee.

፴፰. ለግል ጉዳይ የሚሰጥ ፈቃድ

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ትዳር ሲመሰርት የጋብቻ ፈቃድ አምስት የሥራ ቀናት ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የትዳር ጓደኛ፣ ተወላጅ፣ ወላጅ፣ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ የሞተበት እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት ሦስት ተከታታይ ቀናት የሐዘን ፈቃድ እና ወደ ሐዘኑ ሥፍራ ለሚያደርገው ጉዞ እንደርቀቱ ሁኔታ ተጨማሪ ፈቃድ ይሰጠዋል።

፫/ ማንኛዉም የፖሊስ አባል መደበኛ ሥራው ላይ ሆኖ በትርፍ ጊዜው ለሚማረዉ ትምህርት ከትምህርት ተቋሙ በሚያቀርበው ማስረጃ መሠረት ፈተና የሚወስድበት ጊዜ ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጠዋል።

፴፱. ከደመወዝ ጋር ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

፩/ ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ ለወሰደው ጊዜ፤ ወይም

፪/ በኮሚሽኑ እቅድ መሠረት በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር የሚሰጥ ትምህርት ለመከታተል፤

ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

፵. ያለደመወዝ ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ

ማንኛውም የፖሊስ አባል ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በቂ ምክንያት ሲያቀርብና የኮሚሽኑን ሥራ የማይጎዳ ሲሆን ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

## ክፍል ስድስት
## ስለሕክምና እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች

፵፩. የሕክምና አገልግሎት

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በኮሚሽኑ የሕክምና ተቋሞች ለራሱና ለቤተሰቡ አባላት ነፃ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት ይኖረዋል።

፪/ ለፖሊስ አባል ወይም ለቤተሰቡ አባል የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ከኮሚሽኑ የሕክምና ተቋሞች አቅም በላይ ሲሆን በሌላ የመንግሥት የሕክምና ተቋም በሪፈራል እንዲሰጥ ይደረጋል።

፫/ ለፖሊስ አባል የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት ከኮሚሽኑና ከሌሎች የመንግሥት የሕክምና ተቋማት አቅም በላይ መሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የሪፈራል ሆስፒታል የህክምና ቦርድ ሲረጋገጥ በሀገር ውስጥ በሚገኝ የግል የሕክምና ተቋም በኮሚሽኑ ወጪ እንዲሰጥ ይደረጋል።

38. Leave for Personal Matters

1/ Any police officer shall be entitled to five working days leave with pay when he celebrates his marriage.

2/ Any police officer shall be entitled to mourning leave with pay for three consecutive days in the event of the death of his spouse, descendant, ascendant or any other relative up to the second degree by consanguinity or affinity and may be given additional leave for the time spent on travel depending on the distance of the mourning place.

3/ Any police officer who seats for examination in relation to his part time education shall be granted exam leave with pay, upon production of evidence from the institution where he attends.

39. Special Leave with Pay

Any police officer shall be entitled to special leave with pay where:

1/ he is summoned by a court of law or any other competent authority, for the time utilized for that purpose; or

2/ he attends education offered at home or abroad according to the Commission's plan.

40. Special Leave without Pay

Any police officer may be granted special leave without pay in accordance with directive to be issued by the Commission and upon production of sufficient grounds if such leave does not adversely affect the interests of the Commission.

## PART SIX
## MEDICAL AND OTHER BENEFITS

41. Medical Service

1/ Any police officer shall have the privilege to get free medical service for himself and his family members in the Commission's medical institutions.

2/ Where the medical service to be provided to a police officer or member of his family is beyond the capacity of the Commission's medical institutions, it shall be offered by another public medical institution on the basis of a referral arrangement.

3/ Where the medical service to be provided to a police officer is beyond the capacity of the Commission's medical institutions as well as that of other public medical institutions, as ascertained by the Medical Board of the Federal Police Referral Hospital, it shall be offered by a local private medical institution at the cost of the Commission.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚሰጡ የሕክምና አገልግሎቶች በገዛ ፈቃድ ሥራ መልቀቅን ወይም በዲስፕሊን ወይም በወንጀል ጥፋት ምክንያት መባረርን ሳይጨምር አገልግሎቱ ለተቋረጠ የፖሊስ አባልና ለቤተሰቡ አባላትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፭/ የኮሚሽኑ የሕክምና ተቋሞች አቅም እስከፈቀደ ድረስ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪(፭) በተመለከተው ትርጓሜ የማይሸፈኑ የፖሊስ አባሉ ልጆች እና የፖሊስ አባሉና የትዳር ጓደኛው አባት፣ እናት፣ እህትና ወንድም በክፍያ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## ፵፪. የመኖሪያ ቤትና የትራንስፖርት አገልግሎት

፩/ ኮሚሽኑ አቅም በፈቀደ መጠን የፖሊስ አባላት የመኖሪያ ቤት፣ የትራንስፖርት፣ የውሃና የመብራት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፪/ በሥራ ባህሪያቸው ምክንያት በካምፕ የሚኖሩ የፖሊስ አባላት የቤት፣ የውሃ እና የመብራት አገልግሎት በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

፫/ ለፖሊስ አባል የሚሰጡ የመኖሪያ ቤት፣ የውሃና የመብራት አገልግሎቶች የፖሊስ አባሉን አገልግሎት መቋረጥ ተከትሎ ይቋረጣሉ፤ ሆኖም የፖሊስ አባሉ አገልግሎት የተቋረጠው፡-

ሀ) በግዳጅ ላይ በመሰዋቱ ከሆነ እስከ ሁለት ዓመት፤

ለ) በጡረታ ምክንያት ከሆነ እስከ አንድ ዓመት፤ ወይም

ሐ) በማናቸውም ሌላ ምክንያት ከሆነ እስከ አንድ ወር፤

እንደሁኔታው የፖሊስ አባሉ ወይም ቤተሰቡ እነዚህን አገልግሎቶች የማግኘት መብታቸው ይጠበቅላቸዋል፡፡

## ፵፫. የቀብር ሥነ-ሥርዓት አገልግሎት

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት የሞተ እንደሆነ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ማስፈፀሚያ ወጪ በኮሚሽኑ ይሸፈናል፤ እንዲሁም የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ እንደ ማዕረግ ደረጃው በፖሊሳዊ የክብር የቀብር ሥነ-ሥርዓት ይፈፀማል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ማዕረግ ያለው የፖሊስ አባል ሲሞት ቀብሩ በፖሊሳዊ የቀብር ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይፈጸማል፡፡

4/ The medical benefits under sub-article (1) and (2) of this Article shall also be applicable to a police officer and members of his family after termination of his service, excluding termination as a result of resignation or dismissal on grounds of disciplinary or criminal offence.

5/ Where the capacities of the Commission's medical institutions allow, paid medical services shall be provided to the children of the police officer not covered by the definition provided under Article 2(5) of this Regulation and to the father, mother, sisters and brothers of the police officer and that of his spouse.

## 42. Housing and Transport Services

1/ The Commission shall provide housing, transport, water and electric power supply services to police officers to the extent possible.

2/ Police officers who have to be stationed at camps due to the nature of their duties shall be provided, free of charge, with dwelling units and the supply of water and electricity.

3/ The provision of housing and supply of water and electricity to a police officer shall cease following termination of his service; provided, however, that the police officer or his family, as the case may be, shall be entitle to such benefits up to:

a) two years after termination of his service due to his sacrifice on duty;

b) one year after termination of his service due to retirement; or

c) one month after termination of his service due to any other reason.

## 43. Funeral Service

1/ Where a police officer dies as a result of employment injury, the funeral expense shall be covered by the Commission; and the funeral ceremony shall be conducted with honor depending on his police rank.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article the funeral ceremony of a senior police officer shall be conducted with honor.

## ክፍል ሰባት
## የፖሊስ አባላት ሥነምግባር፣ የኃይል አጠቃቀም እና ግዴታዎች

### ፵፬. የሥነ-ምግባር መርሆዎች

ማንኛዉም የፖሊስ አባል የሚከተሉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች መከተል አለበት፡-

፩/ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት፡-

ሀ) በብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መካከል በዘር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በቀለም፣ በፖለቲካዊ አመለካከት፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ማንኛዉም ምክንያት አድልዎ ሳያደርግ ሕጋዊ መብታቸውን የማክበር እና የማስ ከበር፤

ለ) ሕገ-መንግስቱን፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸ ውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ኮንቬንሽኖች እና ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና የማስከበር፤

ሐ) ማንኛውንም ዓይነት የወንጀል ድርጊት በጽናት የመከላከል እና ራሱም ከወንጀል ድርጊት የመራቅ::

፪/ ሥራዉን በማስተዋል፣ በትህትና፣ በታጋሽነት እና በከፍተኛ ጥንቃቄ የማከናወን፤

፫/ መልካም ሥነምግባርን የሚያጎድሉ አካባቢ ዎች አለማዘዉተር፣ የራሱን እና የተቋሙን ክብር የመጠበቅ፤

፬/ የሥራ ሰዓትን በማክበር ለሌሎች አርአያ የመሆን፤

፭/ አግባብ ባለው ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሀገርንና የሕዝብን ደኅንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን ሚስጥርነት የመጠበቅ፤

፮/ ሥልጣን ባለው ኃላፊ ካልታዘዘ ወይም ከሥራው ባሕሪ አንፃር ጉዳዩን እንዲያውቀው የሚገባው ሰው ካልሆነ በስተቀር የፖሊስን የሥራ እንቅስቃሴ፣ ስምሪት፣ ትጥቅና ተመሳሳይ መረጃዎችን ለማይመለከተው ሰው አለመግለጽ፤

፯/ ከራሱ፣ ከሥጋ ዘመዱ ወይም ከጋብቻ ዘመዱ ጥቅም ጋር የተያያዘ እና ከሥራ ኃላፊነቱ ጋር ግጭት የሚፈጥርበት ጉዳይ ሲያጋጥመው ለአለቃው በጽሁፍ የማሳወቅ እና የጥቅም ግጭቱን ለማስወገድ ከአለቃው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሥራውን የማከናወን፤

፰/ የተመደበበትን መደበኛ ሥራ ዕውቀትና ችሎታውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም የመፈፀም፤

## PART SEVEN
## ETHICS, USE OF FORCE AND DUTIES OF POLICE OFFICERS

### 44. Ethical Principles

Every police officer shall adhere to the following *ethical principles:*

1/ in accordance with the powers and responsibilities given to him:

a) respect and protect the rights of nations, nationalities and peoples without discrimination on the account of race, gender, religion, language, color, political outlook, wealth, birth or any other ground;

b) respect and protect the Constitution and international human right conventions ratified by Ethiopia and other laws;

c) resolutely combat all criminal activities and refrain from involving in such activities.

2/ discharge his duties with consideration, modesty, patience and great care;

3/ avoid frequenting indecent places and preserve his personal and institutional reputations;

4/ be a role model in respecting working hours;

5/ without prejudice to the provision of the relevant law, observe the secrecy of classified information relating to the security of the country and the people;

6/ refrain from disclosing information concerning the operations, deployment, and equipment of the police and any other similar police information to any person except authorized by the competent official or the person should have access to such information because of the nature of his duty;

7/ inform in writing to his superior any conflict of his interest or that of a person related to him by consanguinity or affinity with his responsibility; and discharge his responsibilities in a manner that could avoid the conflict of interest when so directed by his superior;

8/ perform his duties to the best of his knowledge and ability;

፱/ ከበላይ ኃላፊው የሚሰጠውን ማንኛውንም ሕጋዊ ትዕዛዝ የመፈፀም፤
፲/ የበላይ አመራርን የማክበር፤
፲፩/ በአማላጅ አለመሥራትና ራሱም በአማላጅነት አለመቅረብ፤
፲፪/ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላዉ ለማስገኘት ሥልጣኑንና ክብሩን መሣሪያ በማድረግ ያለመጠቀም፤
፲፫/ ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሰጠው ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ከማንኛውም ሰው ያለመቀበል፤
፲፬/ በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ሳይፈቀድ ማንኛውንም ዓይነት መዋጮ ያለማሰባሰብ፡፡

## ፵፭. የኃይል አጠቃቀም

፩/ የፖሊስ አባል ኃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት ግልጽ ተቃውሞ ካጋጠመውና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡፡
፪/ የፖሊስ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጦር መሣሪያ ሊጠቀም የሚችለው፦
ሀ) በራሱ ወይም በሌላ ሰው ላይ ሞት ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት ከሚያደርስ ጥቃት ለመከላከል፤
ለ) በማምለጥ ላይ ያለ አደገኛ የወንጀል ተጠርጣሪ በሕግ ቁጥጥር ስር ለማዋል ወይም ከእስር በማምለጥ ላይ ያለን ተጠርጣሪ ወይም ፍርደኛ ለማስቆም፤
ከጦር መሣሪያ ዉጭ ያሉ ሌሎች እርምጃዎች በቂ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ብቻ ነው፡፡
፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የጦር መሣሪያ የተጠቀመ የፖሊስ አባል፦
ሀ) ጉዳት የደረሰበት ሰው አስቸኳይ የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ ማድረግ፤ እና
ለ) ስለተፈጠረው ሁኔታ ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ፤
አለበት፡፡

## ፵፮. የንብረት አያያዝና አጠቃቀም

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለሥራ የተሰጠውን የመንግሥት ሀብት በአግባቡ የመጠበቅና ለታቀደለት ዓላማ ብቻ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት፡፡
፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው ያለ አመራር የንብረት አያያዝና አጠቃቀምን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

9/ execute any lawful order given to him by his superior;
10/ respect the top management;
11/ avoid working under being lobbied by others, and refrain from lobbying others;
12/ refrain from using his authority and honor to secure undue advantage for himself or for others;
13/ refrain from taking a present or any other benefit directly or indirectly from any person for the service he has delivered or expected to deliver in relation to his duties;
14/ refrain from collecting any contribution in the absence of authorization by the appropriate higher official.

## 45. Use of Force

1/ A police officer may use proportionate force when faced with clear resistance in discharging his duties and where other options are not available.
2/ A police officer may use firearms pursuant to sub-article (1) of this Article only where other measures short of firearms are insufficient to:
a) protect his own life or the life of others from death or from grave bodily injury;
b) apprehend a dangerous criminal suspect or to restrain a suspect or convicted prisoner from escaping.
3/ A police officer who has used firearms pursuant to sub-article (2) of this Article shall:
a) help the injured person to get emergency medical treatment; and
b) forthwith submit a report of the incident to the concerned higher official.

## 46. Handling and Use of Resources

1/ Any police officer shall have the duty to properly handle government resources assigned to him to discharge his duties and use them only for their intended purposes.
2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, any level management shall have the duty to follow up and supervise the handling and use of resources.

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለሥራ ማከናወኛ በተሰጠዉ ሀብት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም መጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱን ወይም መጥፋቱን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ያደረሰ እንደሆነ ነው።

፵፯. ሌላ ሥራ ስለመሥራት

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለኮሚሽኑ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም ከሙያ ግዴታዉ ጋር የሚጋጭ ወይም የማይጣጣም ማናቸውም ሌላ ሥራ መሥራት የለበትም።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖሊስ አባል ኮሚሽኑን አሳዉቆ በትርፍ ጊዜው ሌላ ሥራ መሥራት ይችላል።

፵፰. ለሕክምና ምርመራ ስለመቅረብ

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ በስተቀር ከሥራው ጋር በተያያዘ በቂ ምክንያት የሕክምና ምርመራ እንዲያደርግ በኮሚሽኑ ሲጠየቅ ለምርመራ የመቅረብ ግዴታ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ለሚደረገው የሕክምና ምርመራ የሚያስፈልገው ወጪ በኮሚሽኑ ይሸፈናል።

፵፱. ስለደንብ ልብስ

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) በሥራ ላይ በሚሆንበት ወቅት ንጽህናዉ የተጠበቀ የደንብ ልብሱን አሟልቶ የመልበስና በደንብ ልብሱ ላይ የተፈቀደለትን የማዕረግ ምልክት የማድረግ፤ ወይም

ለ) በሥራ ምድቡ ምክንያት የደንብ ልብስ የማይለብስ ከሆነ በምትኩ የተሰጠውን ልብስ የመልበስ፤

ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የተሰጠውን የደንብ ልብስ ለሌላ ሰው ማዋስ አይችልም።

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የደንብ ልብሱን ሲለብስ ከጋብቻ ቀለበት ዉጭ ጌጣ ጌጥ ማድረግ የለበትም።

፶. በእንክብካቤ መያዝ ስለሚገባቸው ሰዎች

ማንኛውም የፖሊስ አባል ህፃናትን፣ ሴቶችን፣ አረጋውያንና የአካል ጉዳተኞችን ስሜታቸውን በማይነካ ሁኔታ በእንክብካቤ የመያዝ ግዴታ አለበት።

፶፩. ተጠያቂነት

ማንኛውም የፖሊስ አባል ሕግን በመጣስ በሚወስነው ውሳኔ ወይም በሚፈጽመው ድርጊት ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

3/ A police officer shall be liable for the damage or loss of resources assigned to him to discharge his duties if the damage or the loss has resulted from his intentional or negligent act.

47. **Engagement in Another Work**

1/ Any police officer may not engage in any other work which may impair his service or be in conflict or inconsistent with his professional duties.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this Article, a police officer may, after informing the Commission, engage in another work during his leisure time.

48. **Submission for Medical Examination**

1/ Any police officer shall, except for HIV/AIDS test, submit himself for medical examination when required by the Commission for good cause related to his duties.

2/ The cost of medical examination to be carried out in accordance with sub-article (1) of this Article shall be covered by the Commission.

49. **Uniform**

1/ Any police officer shall:

a) wear his clean and complete uniform while on duty and put his rank insignia on the uniform; or

b) wear clothes provided as a replacement if not required to wear uniform due to his position of assignment.

2/ Any police officer may not lend his uniform to other persons.

3/ Any police officer may not wear jewelry, except marriage ring, with his uniform.

50. **Persons to be Treated with Care**

Any police officer shall have the duty to treat children, women, senior citizens and disabled persons with care not to affect their feelings.

51. **Liability**

Any police officer shall be liable for the damages caused as a result of his decision or action in violation of the law.

## ክፍል ስምንት
## የዲስፕሊን እርምጃዎችና ቅሬታ አቀራረብ

**፶፪. የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ**

የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ የፖሊስ አባል በፈፀመው የዲስፕሊን ጥፋት ተጸጽቶ ለወደፊቱ እንዲታረምና ብቁ የፖሊስ አባል እንዲሆን ማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከፖሊስ አባልነት ማሰናበት ነው፡፡

**፶፫. ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች**

ከሚከተሉት ድርጊቶች አንዱን የፈጸመ የፖሊስ አባል በቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡-

፩/ የደንብ ልብስ ከነማዕረግ ምልክቱ አሟልቶ አለመልበስ ወይም ባጅ ወይም የመለያ ቁጥር አለማድረግ፤
፪/ በማዕረግ ለሚበልጠው የፖሊስ አባል ሠላምታ አለመስጠት፤
፫/ የበታች አባላትን ማንቋሸሽ ወይም ማሸማቀቅ፤
፬/ የበላይ ኃላፊን አለማክበር፣ ማንጓጠጥ ወይም ማስፈራራት፤
፭/ በሥራ ቦታ ተገኝቶ ወደ ሥራ አለመሰማራት፤
፮/ በሥራ ሰዓት ተሰብስቦ ማውራት፤
፯/ በፖሊስ አባል የዲስፕሊን ጉድለት መፈጸሙን እያወቀ ለሚመለከተው ክፍል አለማሳወቅ፤
፰/ የግል ንፅህናን ያለመጠበቅ፤
፱/ የደንብ ልብሱን ለብሶ አልባሌ ቦታ መገኘት፤
፲/ በቸልተኝነት የጦር መሣሪያ ጥይት ማባረቅ፤
፲፩/ ያለበቂ ምክንያት ወይም ያለፈቃድ ከሰባት ለማይበልጡ ተከታታይ ቀናት ከሥራ መቅረት፤
፲፪/ ለሥራ አርፍዶ መግባት ወይም መዉጫ ሰዓት ሳይደርስ ቀድሞ ከሥራ መውጣት፤
፲፫/ ባለጉዳይን ተገቢ ባልሆነ ምክንያት በቀጠሮ ማጉላላት፤
፲፬/ የዲስፕሊን እርምጃ የመውሰድ ወይም ክስ የማቅረብ ኃላፊነትን አለመወጣት፤
፲፭/ በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ ክብደት ያለዉ ሌላ የዲስፕሊን ጉድለት መፈፀም፡፡

**ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች**

ከሚከተሉት ድርጊቶች አንዱን የፈጸመ የፖሊስ አባል በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡-

፩/ ቀላል የዲስፕሊን ጥፋትን ከሁለት ጊዜ በላይ በመደጋገም መፈፀም፤
፪/ ትዕዛዝ ባለማክበር፣ በመለገም፣ በቸልተኝነት ወይም የአሠራር ሥነ-ሥርዓትን በመጣስ በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤
፫/ የአባላትን የሥራ አንድነት በሚያናጋ እንቅስቃሴ መሳተፍ ፤

## PART EIGHT
## DISCIPLINARY MEASURES AND GRIEVANCE PROCEDURE

**52. Objectives of Disciplinary Penalties**

The objectives of disciplinary penalties shall be to rehabilitate a delinquent police officer when he can learn from his mistakes and become dependable police officer or to discharge him if he becomes recalcitrant.

**53. Simple Disciplinary Offences**

A police officer who has committed any of the following shall be guilty of simple disciplinary offence:

1/ failure to wear complete uniform with the insignia of rank, badge or identification number;
2/ failure to salute a police officer higher than his rank;
3/ demoralize or harass subordinates;
4/ failure to give due respect to, tease or intimidate a superior;
5/ not to be on duty while being in the work place;
6/ chat in a group during working hours;
7/ failure to notify a breach of discipline by a police officer to the appropriate unit while being aware of the offence;
8/ failure to keep his personal hygiene;
9/ being present at an indecent place while wearing his uniform;
10/ firing arms by negligent handling;
11/ being absent from duty for not more than seven consecutive days without good cause or permission;
12/ tardiness or leaving office early;
13/ mistreat customers through procrastination;
14/ failure to discharge ones responsibility to take disciplinary measure or institute disciplinary charge;
15/ committing any other offence of similar gravity with the offences specified under this Article.

**54. Grave Disciplinary Offences**

A police officer who has committed any of the following shall be guilty of grave disciplinary offence:

1/ repeatedly committing a simple disciplinary offence more than two times;
2/ undermining one's duty by being disobedient, negligent or tardy or by non-observance of working procedures;
3/ participating in activities which destabilize the unity of police officers;

፬/ ሥራ እንዳይሠራ ሆነ ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

፭/ በተከታታይ ከሰባት ቀን በላይ ያለበቂ ምክንያት ከሥራ መቅረት፤

፮/ በሥራ ቦታ ጸብ መጫር ወይም መደባደብ፤

፯/ በልማዳዊ ስካር ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል፤

፰/ በሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ውጪ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፤

፱/ በሀሰት የሐኪም ፈቃድ በመዉሰድ ሌላ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሰማራት፤

፲/ በተገቢዉ አካል ሳይወከል ስለመሥሪያ ቤቱ ጉዳዮች ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ መስጠት፤

፲፩/ በሥራ ቦታ የሃይማኖት ስብከት ማካሄድ ወይም ሃይማኖት ነክ መዝሙሮችን ወይም ስብከቶችን ማሰማት ወይም ምስሎችን መለጠፍ፤

፲፪/ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ በስተቀር ከሥራው ጋር በተያያዘ የጤና ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ያለመሆን፤

፲፫/ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባለማክበር የፍርድ ሥራን ማስተጓጎል፤

፲፬/ የደንብ ልብስ፣ አርማ፣ መታወቂያ፣ ባጅ ወይም የጦር መሣሪያ ለማይገባው ሰው መስጠት ወይም ማዋስ፤

፲፭/ የታጠቀውን መሣሪያ ያለአግባብ መያዝ ወይም መጣል፤

፲፮/ የጦር መሣሪያ በመጠቀም የሥራ ባልደረቦቹን፣ አለቆቹን ወይም ሰላማዊ ሰዎችን ማስፈራራት፤

፲፯/ ጥንቃቄ በጎደለዉ አያያዝ የጦር መሣሪያ ጥይት እንዲባርቅ በማድረግ በሰው አካል፣ ሕይወት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ፤

፲፰/ የሕግ ጥሰትን እያየ በማለፍ የሙያ ግዴታን ያለመወጣት፤

፲፱/ ራሱን ለአደጋ ሳያጋልጥ በፖሊሳዊ ግዳጅ ላይ የቆሰለን የፖሊስ አባል መርዳት ወይም የተሰዋን የፖሊስ አባል አስከሬን ማንሳት ሲችል ትቶ መሄድ፤

፳/ የሰብአዊ መብት ጥሰት ድርጊት መፈጸም ወይም ሕገ-መንግሥቱን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም ወይም ውሳኔ መስጠት፤

፳፩/ ከግዳጅ መሸሽ ወይም ከጥበቃ ቦታ ላይ መጥፋት፤

፳፪/ በሥራ ቦታ ወይም ከሥራ ቦታ ውጪ ፆታዊ ጥቃት መፈፀም፤

4/ deliberately obstructing work or collaborating with others in committing such offence;

5/ being absent from work without good cause for more than seven consecutive days;

6/ instigating or involving in physical violence at the place of work;

7/ neglecting one's duty by being alcoholic or drug addict;

8/ committing acts contrary to public morality in working place or elsewhere;

9/ engaging in other income generating activity *by producing false sick leave;*

10/ giving statement to mass media on the affairs of the Commission without any authorization from the appropriate body;

11/ preaching religion, playing religious songs or teachings or posting religious pictures at the place of work;

12/ refusing to submit oneself to medical examination relating to work, with the exception of HIV/AIDS;

13/ obstructing court proceedings by failing to observe any court order;

14/ giving or lending uniform, emblem, identity card, badge or weapon to a person not entitled;

15/ mishandling or missing a weapon one is armed with;

16/ intimidating colleagues, superiors or civilians by using weapons;

17/ inflicting bodily injury, death or property damage by a bullet fired from negligently mishandled firearm;

18/ disregarding violation of laws and failure to discharge one's duties;

19/ failure to assist a police officer injured on duty or pick up the body of sacrificed police officer, where there is possibility to do so without exposing oneself to danger;

20/ committing an act of human right contravention or performing an act or rendering a decision contrary to the Constitution;

21/ disappearing from duty or abandoning a guard post;

22/ committing sexual harassment in working place or elsewhere;

፳፫/ ጉቦ መቀበል፣ መስጠት ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

፳፬/ በሥራ ቦታም ሆነ ከሥራ ቦታ ዉጭ የስርቆት፣ የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ተግባር መፈፀም፤

፳፭/ በኮሚሽኑ ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

፳፮/ በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፤

፳፯/ ሚስጥር የሆኑ መረጃዎችን ማዉጣት፤

፳፰/ በሌላ ሽፊኒ ወይም የበለጉዳዩን ሰነድ መደ ብሎ ማዘጋጀት፣ ማጥፋት ወይም ማበላሸት፤

፳፱/ በሚቀጠርበት ወቅትም ሆነ ከተቀጠረ በኋላ ሐሰተኛ የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃን ማቅረብ፤

፴/ የኮሚሽኑን ማኅተም፣ ቲተር ወይም አርማ በያዙ ህትመቶችና ቅፆች ወይም በመታወቂያ ወረቀቶች የማጭበርበር ድርጊት መፈፀም ወይም ለመፈፀም መሞከር፤

፴፩/ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ መገኘት ወይም የፖሊቲካ ፓርቲን በመደገፍ ወይም በመቃወም መንቀሳቀስ፤ ወይም

፴፪/ በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሣሣይ ክብደት ያለዉ ሌላ ጥፋት መፈፀም።

## ፶፭. ቀላል ዲስፕሊን ቅጣት

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፫ ከንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፲) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

፪/ ማንኛውም ፖሊስ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ከተቀጣ በኋላ ያንኑ ጥፋት በድጋሚ የፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፫ ከንዑስ አንቀፅ (፲፩) እስከ (፲፬) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ተመሳሳዩን ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ፤

የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

## ፶፮. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት

፩/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፬ ከንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፲፪) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ የፖሊስ አባል የዲስፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ አንድ ወር ደመወዝ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

23/ accepting, giving or soliciting a bribe;

24/ to commit theft, breach of trust or fraudulent acts in the working place or elsewhere;

25/ intentionally or negligently causing damage on the property of the Commission;

26/ abusing one's power;

27/ disclosing classified information;

28/ hiding, transferring to any other person, forging, destroying or damaging documents of the Commission or a customer;

29/ submitting false credential or certificate of experience during or after employment;

30/ committing or attempting to commit fraudulent acts by using the stamps, titers or printed header documents and forms containing the emblem of the Commission or identity cards;

31/ becoming a member of any political party or participating in campaigning for or against a political party; or

32/ committing any other offence of similar gravity with the offences specified under this Article.

## 55. Simple Disciplinary Penalties

1/ Any police officer who commits any of the offences specified from sub-article (1) to (10) of Article 53 of this Regulation or any other similar offence for the first time shall be subject to oral reprimand.

2/ Any police officer who commits:

a) the same offence for the second time after being penalized pursuant to sub-article (1) of this Article; or

b) any of the offences specified from sub-article (11) to (14) of Article 53 of this Regulation or any other similar offence for the first time;

shall be subjected to written warning.

## 56. Rigorous Disciplinary Penalties

1/ Any police officer who commits any of the offences specified from sub-article (1) to (12) of Article 54 of this Regulation or any other similar offence for the first time and found guilty upon conducting disciplinary proceedings shall be subject to a fine up to one month salary.

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ከተቀጣ በኋላ ያንኑ ጥፋት በድጋሚ የፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፬ ከንዑስ አንቀፅ (፲፫) እስከ (፲፱) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ፤

የዲስፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ ሁለት ዓመታት ለሚደርስ ጊዜ የሚቆይ አንድ ደረጃ ከማዕረግ እና ከደመወዝ ዝቅ እንዲል ወይም በኮንስታብል ደረጃ የሚገኝ ከሆነ የማዕረግ እድገት መቆያ ጊዜው እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ እንዲዘገይ በማድረግ ይቀጣል።

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ከተቀጣ በኋላ ያንኑ ጥፋት በድጋሚ የፈጸመ እንደሆነ፤ ወይም

ለ) በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፬ ከንዑስ አንቀፅ (፳) እስከ (፴፩) ከተደነገጉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ለመጀመሪያ ጊዜ የፈፀመ እንደሆነ፤

የዲስፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሰረት ከማዕረግና ከደመወዝ ደረጃ ዝቅ እንዲል ተደርጎ የተቀጣ የፖሊስ አባል የቅጣት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ ከመቀጣቱ በፊት ይዞት የነበረው ማዕረግ እና ደመወዝ ተመልሶ ይሰጠዋል።

**፶፯. ከሥራ ስለማገድ**

፩/ አንድን የፖሊስ አባል ከሥራ አግዶ ማቆየት የሚቻለው፦

ሀ) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክላል፤

ለ) በኮሚሽኑ ሥራ ወይም ንብረት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ያደርሳል፤

ሐ) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንፃር የሌሎች ፖሊስ አባላት ሞራል የሚነካ ይሆናል ወይም ተገልጋዩ ሕብረተሰብ በኮሚሽኑ ላይ ያለውን እምነት ያዛባል፤ ወይም

መ) ተፈፀመ የተባለው ጥፋት ከሥራ ያስወግዳል፤

ተብሎ ሲታመን ነው።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት አንድ የፖሊስ አባል ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ ሊደረግ የሚችለዉ ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል።

2/ Any police officer who commits:

a) the same offence for the second time after being penalized pursuant to sub-article (1) of this Article; or

b) any of the offences specified from sub-article (13) to (19) of Article 54 of this Regulation or any other similar offence for the first time;

and found guilty upon conducting disciplinary proceedings shall be subject to one step demotion in rank and salary for a period extending up to two years or if he is a constable, postponement of his promotion for a period extending up to two years.

3/ Any police officer who commits:

a) the same offence for the second time after being penalized pursuant to sub-article (2) of this Article; or

b) any of the offences specified from sub-article (20) to (31) of Article 54 of this Regulation or any other similar offence for the first time;

and found guilty upon conducting disciplinary proceedings shall be subject to dismissal.

4/ A police officer who has been demoted in accordance with sub-article (2) of this Article shall be restituted to his previous rank and salary upon completion of the penalty period.

**57. Suspension from Duty**

1/ A police officer may be suspended from duty where it is presumed that:

a) he could obstruct the investigation he suspected of by damaging, hiding or destroying evidences relevant to the case;

b) could cause additional damage on the services or property of the Commission;

c) the offence is of such a nature that it would affect the reputation of other police officers or erode the trust that the public had on the Commission; or

d) the offence could lead to dismissal.

2/ The suspension of a police officer and the withholding of his salary pursuant to sub-article (1) of this Article may last for a period not exceeding two months.

፫/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሥራ ሲታገድ የታገደበት ምክንያትና እግዱ የሚቆይበትን ጊዜ የሚገልጽ የእግድ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡

፬/ የፖሊስ አባሉ በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ያልተወሰነበት እንደሆነ በእግድ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

**፶፰. <u>ከስራ የማገድ ሥልጣን</u>**

በዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰን የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ በአንቀፅ ፶፯ መሠረት ከሥራ የማገድ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው፡-

፩/ ተከሳሹ ከኮንስታብል እስከ ዋና ሳጅን ማዕረግ ያለው ሲሆን ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ባለው የበላይ ኃላፊ፤

፪/ ተከሳሹ ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ኢንስፔክተር ማዕረግ ያለው ሲሆን በምክትል ኮሚሽነር ጀነራል፤ ወይም

፫/ ተከሳሹ ከዋና ኢንስፔክተር እስከ ኮሚሽነር ማዕረግ ያለው ሲሆን በኮሚሽነር ጀነራሉ፤

ይሆናል፡፡

**፶፱. <u>የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>**

፩/ ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ የሚወሰደው ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው የፖሊስ አባል የቅርብ አለቃ ይሆናል፡፡

፪/ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃ የሚወሰደው በዲስፕሊን ኮሚቴ በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ ተመሥርቶ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው የፖሊስ አባል ተመድቦ በሚሠራበት ዘርፍ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፫/ በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የተከሰሰ የፖሊስ አባል የጥፋቱን ዝርዝር የሚገልጽ የክስ ቻርጅ እንዲደርሰው ተደርጎ ራሱን የመከላከል በቂ ዕድል ይሰጠዋል፡፡

፬/ በዘርፍ ደረጃ የተቋቋመ የዲስፕሊን ኮሚቴ የክሱን ዝርዝር፣ የተከሳሹን መልስ እና የግራ ቀኙን የሰነድና የሰው ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፮ መሠረት ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ ሃሳብ ለዘርፍ ኃላፊው ያቀርባል፡፡

፭/ የዲስፕሊን ቅጣት ማንኛውንም የፍርድ ቤት ውሣኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፡፡

3/ Where a police officer is suspended from duty he shall be served with a suspension letter stating the grounds and duration of his suspension.

4/ Unless a decision of dismissal is rendered against an accused police officer, the salary withheld at the time of suspension shall be paid to him without interest.

**58. <u>Power to Suspend from Duty</u>**

The power to suspend a police officer in accordance with Article 57 of this Regulation lies in:

1/ a higher official having the rank from Chief Inspector up to Commissioner, where the rank of the accused is from Constable up to Chief Sergeant;

2/ the Deputy Commissioner General, where the rank of the accused is from Assistant Inspector up to Inspector; or

3/ the Commissioner General, where the rank of the accused is from Chief Inspector up to Commissioner.

**59. <u>Taking Disciplinary Measures</u>**

1/ A disciplinary measure against a police officer who is found guilty of a simple disciplinary offence shall be taken by the immediate supervisor of the police officer.

2/ A disciplinary measure against a police officer who is found guilty of a grave disciplinary offence shall be taken, upon the recommendation of a disciplinary committee, by the head of the sector in which the police officer is assigned.

3/ Any police officer accused of grave disciplinary offence shall be served with a disciplinary charge stating the particulars of the offence and shall be given sufficient opportunity to defend himself.

4/ The disciplinary committee, established at the level of a sector, upon establishing guilt after examining the charge, the defense statement of the accused and documentary and witness evidences of the parties, shall submit to the head of the sector its recommendation on the imposition of appropriate penalty in accordance with Article 56 of this Regulation.

5/ Disciplinary penalty may be imposed irrespective of any court proceeding or decision.

## ፷. ይግባኝ ስለማቅረብ

፩/ ቀላል የዲስኘሊን ቅጣት ውሣኔ የተወሰነበት ማንኛውም የፖሊስ አባል በውሣኔው ቅር ከተሰኘ ውሣኔውን ከሰጠው የቅርብ ኃላፊው አንድ ደረጃ ከፍ ለሚለው ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል:: በይግባኝ ውሳኔውም ካልተስማማ ቅሬታውን በደረጃው ከፍ ላለዉ ለሚመለከተው ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፤ በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል::

፪/ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ማንኛውም የፖሊስ አባል በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ የዲስፕሊን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል::

፫/ በዲስፕሊን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም የፖሊስ አባል የይግባኝ ቅሬታውን ለኮሚሽነር ጀነራሉ ማቅረብ ይችላል:: የኮሚሽነር ጀነራሉ ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል::

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማንኛውንም ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የውሣኔው ግልባጭ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ይሆናል::

## ፷፩. የይርጋ ጊዜ

፩/ ቀላል የዲስኘሊን ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል የጥፋቱ መፈጸም ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ካልተቀጣ በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም::

፪/ በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስኘሊን ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል ለእንደዚህ ዓይነት ወንጀሎች ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተደነገገዉ የክስ ማቅረቢያ ይርጋ ጊዜ ዉስጥ የዲስፕሊን ክስ ካልቀረበበት በስተቀር በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም::

፫/ በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስኘሊን ጥፋት የፈፀመ የፖሊስ አባል የጥፋቱ መፈጸም ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ካልተከሰሰ በዲስፕሊን ተጠያቂ አይሆንም::

፬/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ቢኖርም የሚመለከተው የፖሊስ አባል:-

ሀ) ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት መፈጸሙን ባወቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የቅጣት እርምጃ ካልወሰደ፤ ወይም

ለ) ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት መፈጸሙን እያወቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የዲስ ፕሊን ክስ እንዲመሠረት ካላደረገ፤

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) መሠረት በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል::

## 60. Right of Appeal

1/ A police officer against whom a simple disciplinary penalty is imposed may, if he is aggrieved by the decision, appeal to the next higher official. A police officer dissatisfied with the decision made on appeal may again appeal to the next official in the hierarchy; and the decision at this level shall be final.

2/ A police officer against whom a rigorous disciplinary penalty is imposed may appeal to the Commission's Disciplinary Appeal Committee.

3/ A police officer who is dissatisfied by the decision of the Disciplinary Appeal Committee may appeal to the Commissioner General. The decision of the Commissioner General shall be final.

4/ Any appeal under this Article shall be lodged within fifteen days as of the date of receipt of the decision.

## 61. Period of Limitation

1/ A simple disciplinary penalty may not be imposed against a police officer, unless such measure is taken within six months from the date the commission of the offence is known.

2/ No disciplinary charge shall be brought against a police officer who has committed a grave disciplinary offence, which also entails criminal liability, unless such charge is brought within the limitation period of prosecution provided in the Criminal Code for such criminal offence.

3/ No disciplinary charge shall be brought against a police officer who has committed a grave disciplinary offence, which does not entail criminal liability, unless the disciplinary charge is brought within one year from the date the commission of the offence is known.

4/ Any concerned police officer who fails, irrespective of the period of limitation under this Article, to:

a) impose a disciplinary penalty within one month from the date he is aware of the commission of a simple disciplinary offence; or

b) institute a disciplinary charge within three month from the date he is aware of the commission of a grave disciplinary offence;

shall be guilty of a disciplinary offence under sub-article (14) of Article 53 of this Regulation.

፭/ የዲስፕሊን ጥፋትን ለማጣራት የወሰደው ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተካቶ አይታሰብም፡፡

**፷፪. የዲስፕሊን ቅጣት ሪከርድ**

አንድ የፖሊስ አባል በዲስፕሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊጠቀስበት የሚችለው፡-

፩/ ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ፤ ወይም

፪/ ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ፤

ይሆናል፡፡

**፷፫. ስለዲስፕሊን ኮሚቴዎች**

፩/ የከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ክሶችን እየመረመረ የቅጣት ውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የዲስፕሊን ኮሚቴ በእያንዳንዱ ዘርፍ ደረጃ ይቋቋማል፡፡

፪/ የከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ይግባኞችን እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ የኮሚሽኑ የዲስፕሊን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

፫/ የዘርፍ የዲስፕሊን ኮሚቴ ሰብሳቢውን ጨምሮ በኮሚሽኑ የበላይ አመራር የሚመደቡ ሦስት አባላትና አንድ ጸሐፊ እንዲሁም በፖሊስ አባላት የሚመረጡ ሌሎች ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡

፬/ የኮሚሽኑ የዲስፕሊን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢውን ጨምሮ በኮሚሽነር ጀነራሉ የሚሰየሙ አምስት አባላትና አንድ ጸሐፊ ይኖሩታል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) መሠረት የሚፈጸም የኮሚቴ አባላት ምደባና ምርጫ የጾታ ተዋፆን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

፮/ የዲስፕሊን ኮሚቴዎችና የዲስፕሊን ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የሚመሩበት ሥነ ሥርዓት ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## አገልግሎት ስለማቋረጥ

**፷፬. በገዛ ፈቃድ ሥራን መልቀቅ**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል የሰባት ዓመት የግዴታ አገልግሎቱን ከፈፀመ በኋላ የሁለት ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ በመስጠት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ መልቀቅ ይችላል፡፡

5/ The period spent for investigation of a disciplinary offence shall be excluded for computation of the time limit under sub-article (4) of this Article.

**62. Disciplinary Record**

A disciplinary penalty imposed on a police officer shall be cited as a record:

1/ up to one year from the date of imposition, if it is a simple disciplinary penalty; or

2/ up to two years from the date of imposition, if it is a rigorous disciplinary penalty.

**63. Disciplinary Committees**

1/ A disciplinary committee shall be established at the level of each sector to examine charges of grave disciplinary offences and to recommend the imposition of penalties.

2/ The Commission's Disciplinary Appeal Committee shall be established to examine and decide on appeals against rigorous disciplinary penalties.

3/ A sector disciplinary committee shall have three members, including the chairperson, and a secretary to be designated by the senior management of the Commission and two other members to be elected by police officers.

4/ The Commission's Disciplinary Appeal Committee shall have five members, including the chairperson, and a secretary to be designated by the Commissioner General.

5/ The designation and election of members of committees under sub-article (3) and (4) of this Article shall consider gender composition.

6/ The rules of procedures of sector disciplinary committees and the Commission's Disciplinary Appeal Committee shall be determined by directive to be issued by the Commission.

## PART NINE

## TERMINATION OF SERVICE

**64. Resignation of a Police Officer**

1/ Any police officer may resign after having completed his seven years compulsory service and by giving a two-month advance notice in writing.

፪/ የመልቀቂያ ጥያቄው የቀረበው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ወቅትና ሕግን ለማስከበር ልዩ ተልዕኮ በተሰጠበት ጊዜ ውስጥ ከሆነ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እስከሚነሳ ወይም ልዩ ተልዕኮዉ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የመልቀቂያ ጥያቄዉ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንደተነሳ ወይም ልዩ ተልዕኮው እንደተጠናቀቀ የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜው መቆጠር ይጀምራል።

፫/ ኮሚሽኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜው ከማለፉ በፊት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገውን መሠረት አድርጎ የተለየ ውሳኔ ካልሰጠ በስተቀር የመልቀቂያ ጥያቄው እንደተፈቀደ ይቆጠራል።

፬/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) ድንጋጌዎች በመተላለፍ አገልግሎቱን ያቋረጠ የፖሊስ አባል በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰባት ዓመት የግዴታ አገልግሎት ዘመኑን ሳያጠናቅቅ በራሱ ፈቃድ ሥራ የለቀቀ የፖሊስ አባል አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለመሠረታዊ የፖሊስ ትምህርትና ሥልጠና የወጣውን ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት።

፮/ ከመደበኛ ሥራ ውጪ ሆኖ ትምህርት ወይም ሥልጠና ያገኘ የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ መሠረት ማገልገል ያለበትን ጊዜ ሳያጠናቅቅ መልቀቂያ የጠየቀ እንደሆነ አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለትምህርቱ ወይም ለሥልጠናው የወጣውን ወጪ እንዲከፍል ይደረጋል።

፯/ በመደበኛ ሥራ ላይ ሆኖ ትምህርት ወይም ሥልጠና ያገኘ የፖሊስ አባል በዚህ ደንብ መሠረት ማገልገል ያለበትን ጊዜ ሳያጠናቅቅ መልቀቂያ የጠየቀ እንደሆነ አገልግሎት ያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ ለትምህርቱ ወይም ለሥልጠናው የወጣውን ወጪ ግማሽ እንዲከፍል ይደረጋል።

**፷፭. <u>በሕመም ወይም በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት አገልግሎትን ማቋረጥ</u>**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በህመም ወይም በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት የተሰጠው የፈቃድ ጊዜ ካበቃ በኋላ ወደ ሥራው መመለስ አለመቻሉ በሀኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል።

2/ Where the resignation notice is submitted at the time when a state of emergency has been declared and he is on special mission, his resignation may not be accepted until the state of emergency is lifted or the special mission is completed; provided, however, that the two months notice period shall commence to count after the state of emergency is lifted or the special mission is completed.

3/ The resignation shall be deemed to have been accepted unless the Commission decides otherwise on the basis of the provisions of sub-article (2) of this Article within the notice period.

4/ A police officer who has terminated his service in contravention of the provisions of sub-article (1) or (2) of this Article shall be criminally liable.

5/ Without prejudice to the provisions of sub-article (4) of this Article, a police officer who has resigned before having completed his seven years compulsory service shall pay back the portion of the cost of his basic police education and training corresponding to the remaining balance of the compulsory service period.

6/ Where a police officer who has received off job education or training submits notice of resignation before the completion of the service period required under this Regulation, he shall pay back the portion of his education or training cost corresponding to the remaining balance of the required service period.

7/ Where a police officer who has received on job education or training submits notice of resignation before the completion of the service period required under this Regulation, he shall pay back half of the portion of his education or training cost corresponding to the remaining balance of the required service period.

**65. <u>Termination on Grounds of Illness or Employment Injury</u>**

1/ The service of any police officer who is unable, as confirmed by a medical board, to resume work after completing his sick or employment injury leave shall be terminated.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የፖሊስ አባል አግባብ ባላቸው የጡረታ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት መብቱ ይጠበቅለታል።

፫/ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት ምልምል የፖሊስ ሠልጣኝ ሊድን የማይችል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ በሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጦ ሲሰናበት በስልጠና ላይ እያለ ይከፈለው የነበረው የአንድ ዓመት የሥልጠና አበልና የመጓጓዣ ወጪ ተከፍሎት ይሰናበታል።

## ፷፮. በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ለተመደበበት ሥራ ያለውን ዕውቀትና ችሎታ ተጠቅሞ ለመሥራት የተቻለውን ጥረት እያደረገ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ከአማካይ ነጥብ በታች የሆነ እንደሆነ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ቀደም ባሉት ተከታታይ አምስት ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ሲያስመዘግብ የነበረ የፖሊስ አባል የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለሦስት ዓመታት ከአማካይ ነጥብ በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ እንዲሰናበት አይደረግም።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ወይም (፪) መሠረት አንድን የፖሊስ አባል ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው፦

ሀ) ለያዘው የሥራ መደብ የሚያስፈልገውን ሥልጠና በመስጠት፤ ወይም

ለ) ከያዘው የሥራ ደረጃ ጋር ተመሳሳይ በሆነና ሊሠራው ወደሚችለው ሌላ የሥራ መደብ በማዛወር፤

ከአንድ ዓመት ለማያንስ ጊዜ እንዲሰራ ተደርጎ ብቃቱን ማሻሻል ያልተቻለ ከሆነና የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ይሆናል።

## ፷፯. በዲስፕሊን ምክንያት ከሥራ ስለማሰናበት

ማንኛውም የፖሊስ አባል አግባብ ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ተከሶ ከሥራ እንዲሰናበት የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ አገልግሎቱ ይቋረጣል።

## ፷፰. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ

፩/ የማንኛውም የፖሊስ አባል አገልግሎት በአዋጁ አንቀፅ ፲፯ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና በዚህ ደንብ አንቀፅ ፸፩ መሠረት ካልተራዘመ በስተቀር የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰበት የመጨረሻ ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል።

፪/ የፖሊስ አባሉ ጡረታ ከመውጣቱ ከስድስት ወር በፊት በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፤ የመጨረሻዎቹን ሁለት ወራት ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል።

2/ A police officer whose service has been terminated in accordance with sub-article (1) of this Article shall be entitled to the benefits provided for under the relevant provisions of the pension law.

3/ Where an employment injury sustained by a recruit police trainee results in his discharge due to his permanent incapacity, as certified by medical board, he shall be entitled to payment of his one year's training allowance and transport cost.

## 66. Termination on Grounds of Inefficiency

1/ Any police officer whose performance evaluation of two successive years is below satisfactory, despite exerting all his knowledge and ability to accomplish his work shall be discharged.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a police officer who scored high performance evaluation results for the last five successive year may not be discharged on grounds of inefficiency unless his performance evaluation result becomes below satisfactory for the following three successive years.

3/ The termination of service under sub-article (1) or (2) of this Article shall be effected by giving a one month advance notice to the police officer where he is unable to improve his performance at least within a year after:

a) obtaining training required to improve his skills; or

b) being transferred to another suitable position of an equivalent grade.

## 67. Termination on Disciplinary Grounds

The service of any police officer shall be terminated upon final decision of penalty imposing dismissal on the ground of disciplinary charge involving grave disciplinary offence in accordance with the relevant provisions of this Regulation.

## 68. Retirement

1/ The service of a police officer shall, unless extended in accordance with sub-article (2) of Article 17 of the Proclamation and Article 71 of this Regulation, be terminated on the last day of the last month in which he attained the retirement age.

2/ A police officer shall be notified of his retirement in writing six months prior to his retirement and shall be entitled to paid leave for the last two months.

**፷፱. በሞት ምክንያት የአገልግሎት መቋረጥ**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሞተበት ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፪/ አገልግሎቱ በሞት ምክንያት የተቋረጠ የፖሊስ አባል የሞተበት ወር ሙሉ ደመወዝ ለተመዘገበ የትዳር ጓደኛ ወይም የተመዘገበ የትዳር ጓደኛ ከሌለው ለህጋዊ ወራሾቹ ይከፈላል፡፡

፫/ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሞት የተለየ የፖሊስ አባል ተተኪዎች፡-

ሀ) የሞተው በግዳጅ ላይ እያለ በመሰዋቱ ምክንያት ከሆነ የ፲፪ ወር ደመወዙ፤ ወይም

ለ) የሞተው በሌላ ምክንያት ከሆነ የስድስት ወር ደመወዙ፤

በአንድ ጊዜ እንዲከፈላቸው ይደረጋል፡፡

**፸. የሥራ ልምድ ማስረጃ**

ማንኛውም የፖሊስ አባል በሥራ ላይ እያለ ወይም አገልግሎቱ ከተቋረጠ በኋላ በማናቸውም ጊዜ የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑን እና ሲከፈለው የነበረውን ወርሃዊ ደመወዝ የሚገልፅ የሥራ ልምድ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

**፸፩. አገልግሎት ስለማራዘም**

በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የአንድን የፖሊስ አባል አገልግሎት ዘመን ከጡረታ እድሜ በኋላ ማራዘም የሚቻለው፡-

፩/ የፖሊስ አባሉ ትምህርት፣ ዕውቀት፣ ልዩ ሙያ፣ የሥራ ልምድና ችሎታ ለኮሚሽኑ ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤

፪/ በዕድገት፣ በምደባ፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ተተኪ የፖሊስ አባል ለማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፤

፫/ የፖሊስ አባሉ ለሥራዉ ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

፬/ የፖሊስ አባሉ አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ፤ እና

፭/ የአገልግሎቱ ዘመን መራዘም ለኮሚሽነር ጄነራሉ ቀርቦ ሲፈቀድ፤

ይሆናል፡፡

**፸፪. ተመልሶ አገልግሎት ስለመቀጠል**

በዚህ ደንብ መሠረት በገዛ ፈቃዱ ሥራውን የለቀቀ የፖሊስ አባል አገልግሎቱን እንደገና ለመቀጠል ሲያመለክት መመለሱ ከኮሚሽኑ የሰው ኃይል ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ከተገኘና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ሀ)፣ (ለ)፣ (መ)፣ (ሠ)፣ (ሸ)፣ (በ) እና (ተ) የተመለከቱትን መሥፈርቶች አሟልቶ እንደቀጠለ ከሆነ ተመልሶ አገልግሎት እንዲቀጥል ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

**69. Termination upon Death**

1/ The service of any police officer shall terminate upon his death.

2/ Where the service of a police officer is terminated upon his death, the full salary of the month in which he died shall be paid to his registered spouse or in the absence of such spouse to his legal heirs.

3/ Without prejudice to the provisions of the relevant pension law, survivors of a deceased police officer shall be entitled to a lump sum payment of:

a) his 12 months' salary where he has sacrificed his life while on duty; or

b) his six months' salary where he has died of other causes.

**70. Certificate of Service**

A police officer shall be provided with a certificate of service showing the type and duration of his service and his salary when he so requests at any time during his service tenure or after its termination.

**71. Extension of Service**

The service of a police officer may be extended beyond the age of retirement in accordance with sub-article (2) of Article 17 of the Proclamation where:

1/ his qualification, knowledge, special skill, experience and capability is found to be critical to the Commission;

2/ it is ascertained impossible to replace him by another police officer through promotion, assignment, transfer or recruitment;

3/ he is proved medically fit for service;

4/ he has agreed to the extension of his service; and

5/ the extension is approved by the Commissioner General.

**72. Return to Service**

Where a police officer who has resigned in accordance with this Regulation applies to return to service and where his re-engagement meets the human resource needs of the Commission, he may be allowed to return to service subject to his fulfillment of the requirements stipulated under paragraph (a), (b), (d), (e), (h), (j) and (k) of sub-article (1) of Article 4 of this Regulation.

**፸፫. በወንጀል ስለተከሰሰ የፖሊስ አባል**

፩/ ኮሚሽኑ አንድ የፖሊስ አባል በወንጀል የተከሰሰው የሥራ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሲል በፈጸመው ድርጊት ምክንያት መሆኑን ሲያምን፦

ሀ) በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ የራሱን የሕግ ባለሙያ በመመደብ ወይም ጠበቃ በመቅጠር ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፤

ለ) ክርክሩ በሂደት ላይ እያለ የፖሊስ አባሉ በተፈለገበት ጊዜ ፍርድ ቤት ለመቅረብ እንዲችል ዋስ ይሆንለታል፤

ሐ) የዋስ መብቱ የተከበረለት እንደሆነ በሥራው ላይ ሆኖ ደመወዝ እያገኘ ክርክሩን እንዲያካሂድ ያደርጋል፤

መ) ፍርድ ቤቱ የሚያስችልበት ቦታ ከአምስት ኪሎ ሜትር በላይ የሚርቅ ከሆነ በቀጠሮው ቀን ለመቅረብ እንዲችል የመጓጓዣ ወጪና የውሎ አበል ይከፍለዋል፤

ሠ) የዋስ መብቱ ሳይከበርለት ቀርቶ ታስሮ እያለ ክርክሩ የሚካሄድ ቢሆን በፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ደመወዙን ይከፍለዋል፤

ረ) በነፃ በመለቀቁ ወይም የወንጀል ክሱ በመነሳቱ ከእስር ከተፈታ ወደ ሥራው ይመልሰዋል፤

ሰ) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአምስት ዓመት ያልበለጠ የእስራት ቅጣት ከተወሰነበት ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላ ወደ ሥራው እንዲመለስ ያደርጋል፤ ሆኖም በእስር ላይ የቆየበት ጊዜ ደመወዙ አይከፈለውም፤

ሸ) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአምስት ዓመት በበለጠ እስራት እንዲቀጣ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ ውሣኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሥራ እንዲሰናበት ያደርጋል።

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በወንጀል የተከሰሰው የሥራ ኃላፊነቱን ከመወጣት ጋር ግንኙነት በሌለው ሁኔታ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ሲሆን በዚህ ደንብ መሠረት ሊወሰድበት የሚችለው የዲስፕሊን እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

**73. Police Officer Accused of an Offence**

1/ Where a police officer is accused of an offence due to an act committed with a view to discharging his duties, the Commission shall:

a) provide the police officer with free legal service through the assignment of its lawyer or the hiring of the service of an advocate until the final disposal of the case by the court of law;

b) act as a guarantor to secure the release of the police officer on bail;

c) place the police officer on his duty and pay his salary while attending the trial proceedings upon release on bail;

d) pay transportation cost and per diem to the police officer to appear before the court, if the court is far from the working place by more than five kilometers;

e) pay the police officer his salary until the final disposal of the case by the court if he is denied release on bail;

f) place the police officer on his duty where he is released upon acquittal or withdrawal of the charge;

g) where the police officer is convicted and sentenced for a period not exceeding five years, allow him to resume his duty after serving the sentence; provided, however, that unpaid salary during the sentence period may not be claimed;

h) where the police officer is convicted and sentenced, by final court decision, to imprisonment for a period exceeding five years, terminate his service as of the date of the court decision.

2/ Without prejudice to the disciplinary measures to be taken in accordance with this Regulation, if any police officer is accused of an offence due to the commission of an act not related to the discharging of his duties:

ሀ) የዋስ መብቱ የተከበረለት እንደሆነ በሥራው ላይ ሆኖ ደመወዝ እያገኘ ክርክሩን እንዲያካሂድ ይደረጋል፤

ለ) የዋስ መብቱ ሳይከበርለት ቀርቶ ታስሮ እያለ ክርክሩ የሚካሄድ ቢሆን ደመወዙ አይከፈለውም፤

ሐ) በነፃ በመለቀቁ ወይም የወንጀል ክሱ በመነሳቱ ከእስር ከተፈታ ወደ ሥራው የመመለስ መብቱ ይጠበቅለታል፤

መ) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአንድ ዓመት ያልበለጠ የእስራት ቅጣት ከተወሰነበት ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላ ወደ ሥራው የመመለስ መብቱ ይጠበቅለታል፤ ሆኖም በእስር ላይ የቆየበት ጊዜ ደመወዙ አይከፈለውም፤

ሠ) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ ከአንድ ዓመት በበለጠ እስራት እንዲቀጣ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ ውሣኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሥራ እንዲሰናበት ይደረጋል።

## ክፍል አሥር
## የፖሊስ አባላት መረጃ

### ፸፬. የግል ማህደር

፩/ ኮሚሽኑ ስለእያንዳንዱ የፖሊስ አባል አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የሚይዝ የግል ማህደር በማደራጀት በጥንቃቄ የመያዝ ኃላፊነት አለበት።

፪/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኙትን መረጃዎች የመመልከት ወይም ቅጃቸውን የመውሰድ መብት ይኖረዋል።

፫/ በሕግ ስልጣን ባለው አካል ወይም በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ካልታዘዘ በስተቀር ወይም ከሚመለከታቸው የአስተዳደር ሠራተኞች በስተቀር ማንኛውም ሰው የአንድን የፖሊስ አባል የግል ማህደር ማየት አይችልም።

፬/ የፖሊስ አባሉ እንዲያውቀው ያልተደረገን ማንኛውም ዓይነት የሰነድ ማስረጃ በግል ማህደሩ ውስጥ ማስቀመጥ ክልክል ነው።

፭/ ማንኛውም የፖሊስ አባል፡-

ሀ) ጋብቻ ወይም ፍቺ ሲፈፅም የጋብቻውን ወይም የፍቺውን ማስረጃ ለክፍሉ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፤

ለ) ልጅ ሲወለድ ወይም ጉዲፈቻ ሲያደርግ ወይም ከቤተሰቡ አባል አንዱ በሞት ሲለየው ለክፍሉ ማሳወቅ አለበት።

a) he shall be placed on his duty and paid his salary while attending the trial proceedings upon release on bail;

b) he may not be entitled to payment of salary if he is denied release on bail;

c) he shall be entitled to be placed on his duty where he is released upon acquittal or withdrawal of the charge;

d) he shall be allowed to resume his duty after serving the sentence where convicted and sentenced for a period not exceeding one year; provided, however, that unpaid salary during the sentence period may not be claimed;

e) his service shall be terminated where convicted and sentenced, by final court decision, to imprisonment for a period exceeding one year, as of the date of the court decision.

## PART TEN
## RECORDS OF POLICE OFFICERS

### 74. Personnel Records

1/ The Commission shall have the responsibility to keep personnel records containing all relevant information regarding each police officer.

2/ A police officer shall have the right to access to all information contained in his personnel records or to have a copy thereof.

3/ No person except those ordered by law or authorized by appropriate officials of the Commission or the administrative staff shall have access to the personnel records of a police officer.

4/ It is prohibited to deposit any documentary evidence in the personnel records of a police officer without his knowledge.

5/ Any police officer shall:

a) submit evidence of his marriage or divorce to his unit when he concludes a marriage or divorce;

b) notify to his unit the birth or adoption of a child or death of his family member.

**፸፭. ስታትስቲካዊ መረጃዎች**

፩/ ኮሚሽኑ፦
- ሀ) የሰው ሀብት መረጃ ቋት በማዕከል ያደራጃል፤
- ለ) የሰው ሀብት ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት በወጥነት እንዲተገበር ያደርጋል፤
- ሐ) የፖሊስ አባላትን የሚመለከቱ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ለአስፈላጊው ሥራ ጥቅም ላይ ያውላል።

፪/ ማንኛውም የሥራ ዘርፍ በማዕከል ለተደራጀው የሰው ሀብት መረጃ ቋት መረጃዎችን ወቅቱን ጠብቆ የመላክ ግዴታ አለበት።

**፸፮. የሥራ አፈፃፀም ምዘና**

፩/ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ዓላማ፦
- ሀ) የፖሊስ አባላት ሥራቸውን በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ ፍጥነትና ወጪ እንዲያከናውኑ የማስቻል፤
- ለ) የፖሊስ አባላትን ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በመለየት በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የአቅም ግንባታ ሥራ ለመሥራት የማስቻል፤
- ሐ) የፖሊስ አባላት የወደፊት የሥራ አፈፃፀማቸውን እንዲያሻሽሉ የሥራ ተነሣሽነታቸውን የማጎልበት፤
- መ) ለፖሊስ አባላት በውጤት ላይ የተመሠረተ ማትጊያ ለመስጠት የማስቻል፤ እና
- ሠ) አመራሩ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንዲሰጥ የማስቻል፤

ይሆናል ።

፪/ የሥራ አፈፃፀም ምዘና በግልፅና ሥራው የሚመለከታቸው አካላትና የፖሊስ አባሉ በተገኙበት በጋራ የሚከናወን ይሆናል።

፫/ የፖሊስ አባል ከሚማርበት ወይም ከሚሰለጥንበት ተቋም ለኮሚሽኑ የሚላከው ሪፖርት እንደ ሥራ አፈፃፀም ምዘና ሪፖርት ይወሰዳል።

## ክፍል አሥራ አንድ
## የፖሊስ ሽልማቶች

**፸፯. ጠቅላላ**

ሽልማቶች የሚሰጡበት ዓላማ ከፍተኛ አስተዋፆ ያበረከቱና ረጅም ጊዜ አገልግሎት የሰጡ የፖሊስ አባላትን በማበረታታት የኮሚሽኑን ተልዕኮ ስኬት ለማረጋገጥ ይሆናል።

**፸፰. የፖሊስ ሽልማት ዓይነቶች**

፩/ የፖሊስ ሽልማቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፦
- ሀ) የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤
- ለ) የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፤
- ሐ) የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፤
- መ) የላቀ ሥራ ውጤት ሜዳይ፤
- ሠ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ፤

**75. Statistical Data**

1/ The Commission shall:
- a) organize central human resource data base;
- b) implement standardized human resource management information system;
- c) collect and compile statistical data relating to police officers for appropriate use.

2/ Any sector of the Commission shall have the obligation to submit human resource information timely to the central data base.

**76. Performance Evaluation**

1/ The objective of performance evaluation shall be to:
- a) enable police officers to discharge their duties in the required volume, quality, speed and cost;
- b) enable to identify the strength and weakness of police officers and thereby to implement appropriate capacity building programs based on plans;
- c) enable police officers to improve their performance by enhancing their self-motivation;
- d) enable to provide incentives to police officers based on the results; and
- e) enable the management body to make administrative decisions based on tangible information.

2/ Performance evaluation shall be carried out in a transparent manner with the participation of the concerned bodies and the police officer.

3/ A report sent to the Commission by an institution in which a police officer is attending education or training shall be taken as performance evaluation report.

## PART ELEVEN
## POLICE AWARDS

**77. General**

The objectives of awarding prizes shall be to ensure the success of the mission of the Commission through encouraging police officers with outstanding achievements and long years of service.

**78. Types of Police Awards**

1/ Police awards shall be the following:
- a) Medal of Heroism 1st Rank;
- b) Medal of Heroism 2nd Rank;
- c) Medal of Heroism 3rd Rank;
- d) Medal of Distinguished Labour;
- e) Medal of Police Service 1st Rank;

ረ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ፣

ሰ) የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ፣ እና

ሸ) የፖሊስ አገልግሎት ሪባን፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሽልማቶች ቅርፅ፣ ቀለምና ይዘት ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፸፱. የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ**

፩/ የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀው በላይ እጅግ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

፪/ የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የብር ፳ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ፳፭ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣ የተሰዋ እንደሆነ ለሕጋዊ ወራሾቹ ብር ፳፭ሺ ይከፈላል፣

ለ) በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የጀግንነት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የሥራ ክፍል ብር ፳ሺ እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ የተሸላሚው ቡድን ወይም የሥራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም ፳፭ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

**፹. የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ**

፩/ የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀው በላይ በጣም የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

፪/ የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የብር ፲፭ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ፳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፣ የተሰዋ እንደሆነ ለሕጋዊ ወራሾቹ ብር ፳ሺ ይከፈላል፣

ለ) በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የጀግንነት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የሥራ ክፍል ብር ፲፭ሺ እና በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ የተሸላሚው ቡድን ወይም የሥራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም ፳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

f) Medal of Police Service 2nd Rank;

g) Medal of Police Service 3rd Rank; and

h) Police Service Ribbon.

2/ The shape, color and substance of the awards referred to in sub-article (1) of this Article shall be determined by directive to be issued by the Commission.

**79. Medal of Heroism 1st Rank**

1/ The Medal of Heroism 1st Rank is an award that may be bestowed upon a police officer, team or unit that has, beyond the call of ordinary duty, achieved unparalleled feats of bravery.

2/ A police officer awarded with the Medal of Heroism 1st Rank shall:

a) be entitled to a lump sum payment of Birr 20,000 and 25% salary increment; where he is sacrificed his survivors shall be entitled to payment of Birr 25,000;

b) receive a certificate signed by the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3/ A team or unit awarded with the Medal of Heroism 1st Rank shall be entitled to a lump sum payment of Birr 20,000 and a certificate signed by the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. Every police officer who is a member of such team or unit shall be entitled to a 25% salary increment.

**80. Medal of Heroism 2nd Rank**

1/ The Medal of Heroism 2nd Rank is an award that may be bestowed upon a police officer, team or unit that has, beyond the call of ordinary duty, achieved very commendable feats of bravery.

2/ A police officer awarded with the Medal of Heroism 2nd Rank shall:

a) be entitled to a lump sum payment of Birr 15,000 and 20% salary increment; where he is sacrificed his survivors shall be entitled to payment of Birr 20,000;

b) receive a certificate signed by the Commissioner General.

3/ A team or unit awarded with the Medal of Heroism 2nd Rank shall be entitled to a lump sum payment of Birr 15,000 and a certificate signed by the Commissioner General. Every police officer who is a member of such team or unit shall be entitled to a 20% salary increment.

**፹፩. የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ**

፩/ የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ የዘወትር ፖሊሳዊ ግዳጅ ከሚጠይቀው በላይ የሚያኮራ ጀግንነት ለፈፀመ የፖሊስ አባል፣ ቡድን ወይም የስራ ክፍል የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

፪/ የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የብር ፲ሺ የአንድ ጊዜ ክፍያና የ፲፭ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፤ የተሰዋ እንደሆነ ለሕጋዊ ወራሾቹ ብር ፲፭ሺ ይከፈላል፤

ለ) በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የጀግንነት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የሥራ ክፍል ብር ፲ሺ እና በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ የተሸላሚው ቡድን ወይም የሥራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም የ፲፭ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

**፹፪. የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ**

፩/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ በአዕምሮ ሥራ፣ በፈጠራ ወይም በማናቸውም መስክ የኮሚሽኑን ተልዕኮ ለማሳካት የላቀ ውጤት ላስገኘ አባል ወይም የሥራ ክፍል ወይም ቡድን የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

፪/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል፡-

ሀ) የአንድ ደረጃ የማዕረግ እድገትና የ፳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፤ ሽልማቱን ሳይቀበል የሞተ እንደሆነ ለሕጋዊ ወራሾቹ ብር ፰ሺ ይከፈላል፤

ለ) በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የላቀ የሥራ ውጤት ሜዳይ ተሸላሚ የሆነ ቡድን ወይም የሥራ ክፍል በኮሚሽነር ጀነራሉ የተፈረመ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፤ የተሸላሚው ቡድን ወይም የሥራ ክፍል አባል የሆነ እያንዳንዱ የፖሊስ አባልም የአንድ ደረጃ የማዕረግ እድገትና የ፳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠዋል፡፡

**፹፫. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ**

፩/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ በሥነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲስፕሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከሃያ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው፡፡

፪/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ አንደኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የአራት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል፡፡

**81. Medal of Heroism 3rd Rank**

1/ The Medal of Heroism 3rd Rank is an award that may be bestowed upon a police officer, team or unit that has, beyond the call of ordinary duty, achieved commendable feats of bravery.

2/ A police officer awarded with the Medal of Heroism 3rd Rank shall:

a) be entitled to a lump sum payment of Birr 10,000 and 15% salary increment; where he is sacrificed his survivors shall be entitled to payment of Birr 15,000;

b) receive a certificate signed by the Commissioner General.

3/ A team or unit awarded with the Medal of Heroism 3rd Rank shall be entitled to a lump sum payment of Birr 10,000 and a certificate signed by the Commissioner General. Every police officer who is a member of such team or unit shall be entitled to a 15% salary increment.

**82. Medal of Distinguished Labour**

1/ The Medal of Distinguished Labour is an award that may be bestowed upon a police officer, team or unit that has, through mental labour, by way of invention or in any other field, scored distinguished achievement for the success of the mission of the Commission.

2/ A police officer awarded with the Medal of Distinguished Labour shall:

a) be entitled to one step promotion in rank and 20% salary increment; where he dies prior to receiving the award, his survivors shall be entitled to payment of Birr 8,000;

b) receive a certificate signed by the Commissioner General.

3/ A team or unit awarded with the Medal of Distinguished Labour shall receive a certificate signed by the Commissioner General. Every police officer who is a member of such team or unit shall be entitled to one step promotion in rank and 20% salary increment.

**83. Medal of Police Service 1st Rank**

1/ The Medal of Police Service 1st Rank is an award that may be bestowed upon any police officer who is reputed for his spotless record of conduct and police discipline and has served as a police officer for not less than twenty five years.

2/ A police officer awarded with the Medal of Police Service 1st Rank shall be entitled to a lump sum payment of an amount equivalent to his four months' salary.

**፹፬. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ**

፩/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ በሥነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲስፕሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከሃያ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው ::

፪/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሁለተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የሦስት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል ::

**፹፭. የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ**

፩/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ በሥነ-ምግባሩና በፖሊሳዊ ዲስፕሊኑ እንከን ለሌለበትና በፖሊስ አባልነት ከአሥራ አምስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ ላገለገለ የፖሊስ አባል የሚሰጥ ሽልማት ነው።

፪/ የፖሊስ አገልግሎት ሜዳይ ሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ የሆነ የፖሊስ አባል የሁለት ወር ደመወዙን የሚያህል ገንዘብ በአንድ ጊዜ ክፍያ ይሰጠዋል።

**፹፮. የፖሊስ አገልግሎት ሪባን**

የፖሊስ አገልግሎት ሪባን ለሕገ-መንግሥቱ ታማኝ በመሆን በፖሊስ አባልነት ለተሰጠ ለእያንዳንዱ አስር ዓመት አገልግሎት የሚሰጥ ሽልማት ነው።

**፹፯ የሜዳዮችና ሪባኖች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ**

በዚህ ደንብ የተመለከቱት ሜዳዮችና ሪባኖች አሰጣጥ ሥርዓትና አለባበስ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፹፰. ሜዳይና ሪባን መልሶ ስለመውሰድ**

ተሸላሚው:-

፩/ ሜዳዩ ወይም ሪባኑ የተሰጠው በሀሰተኛ ማስረጃ ላይ ተመሥርቶ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም

፪/ በሕገ መንግሥቱ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ በሚደረግ ወንጀል፣ በክዳት፣ በአሸባሪነት፣ አደገኛ ዕፅ በማዘዋወር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲረጋገጥ፤

የተሰጠው ሜዳይ ወይም ሪባን ይወሰድበታል።

**84. Medal of Police Service 2nd Rank**

1/ The Medal of Police Service 2nd Rank is an award that may be bestowed upon any police officer who is reputed for his spotless record of conduct and police discipline and has served as a police officer for not less than twenty years.

2/ A police officer awarded with the Medal of Police Service 2nd Rank shall be entitled to a lump sum payment of an amount equivalent to his three months' salary.

**85. Medal of Police Service 3rd Rank**

1/ The Medal of Police Service 3rd Rank is an award that may be bestowed upon any police officer who is reputed for his spotless record of conduct and police discipline and has served as a police officer for not less than fifteen years.

2/ A police officer awarded with the Medal of Police Service 3rd Rank shall be entitled to a lump sum payment of an amount equivalent to his two months' salary.

**86. Ribbon of Police Service**

The Ribbon of Police Service shall be awarded to each police officer of the Commission every ten years for service given being loyal to the Constitution.

**87. Awarding Ceremony and Wearing of Medals and Ribbons**

The awarding ceremony and wearing of Medals and Ribbons provided under this Regulation shall be prescribed by directive to be issued by the Commission.

**88. Deprivation of Medals and Ribbons**

An awardee of a medal or ribbon shall be deprived of the medal or ribbon where:

1/ it is discovered that the award granted on the basis of false evidence; or

2/ the awardee has been convicted by a court for a crime of outrage against the Constitution or the constitutional order, treason, terrorism, drug trafficking or any other similar crime.

፹፱. ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ ስለሞተ የፖሊስ አባል

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት ለሜዳይ ሽልማት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ የሞተ የፖሊስ አባል አግባብ ያለው ሜዳይ በስሙ ይመዘገብለታል።

፪/ ሜዳዩ ለባለቤቱ ይሰጣል፤ ባለቤት ከሌለው ለታላቅ ልጁ ይሰጣል፤ ልጅ ከሌለው አግባብ ባለው የውርስ ሕግ መሠረት ለውርስ ባለመብቱ ይሰጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የጀግንነት ሜዳይ በስሙ የተመዘገበለት የተሰዋ የፖሊስ አባል የማዕረግ እድገትም ተሰጥቶት በስሙ ሊመዘገብለት ይችላል።

## ክፍል አሥራ ሁለት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፺. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት

ኮሚሽኑ የፖሊስ አባላትን ቅሬታ በአግባቡ ለመፍታት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ይዘረጋል።

፺፩. የአካል ብቃትና ስፖርታዊ ውድድር

ኮሚሽኑ የፖሊስ አባላት በአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችና በስፖርታዊ ውድድሮች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፺፪. ከሕዝብ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

ማንኛውም የፖሊስ አባል፦

፩/ ከማኅበረሰቡ ጋር በሚኖረው ግንኙነት የማኅበረሰቡን ወግ፣ ባህል፣ እምነት እና ማንነት የማክበር፤ እና

፪/ በሕዝባዊ በዓላት አከባበር ላይ የደንብ ልብሱን ለብሶ በመገኘት ሕግና ሥርዓት የማስከበር፤

ኃላፊነት ይኖርበታል።

፺፫. የተከለከሉ ድርጊቶች

ለማንኛውም የፖሊስ አባል የሚከተሉትን መፈጸም የተከለከለ ነው፦

፩/ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፤

፪/ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወይም መሳተፍ፤

፫/ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ወይም ደጋፊ መሆን ወይም የፖለቲካ ድርጅትን በመቃወም አቋም መያዝ፤

፬/ በማንኛውም ሁኔታ በስውርም ይሁን በግልፅ የፖለቲካ ቅስቀሳ ማድረግ፤

፭/ ለምርጫ የሚወዳደር ማንኛውም ፖለቲካ ድርጅት ወይም ሰው በመደገፍም ይሁን በመቃወም ቅስቀሳ ማድረግ ወይም የማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ዓርማ ወይም ለምርጫ የሚጠቀምበትን ምልክት በማንኛውም ቦታ መያዝ ወይም መጠቀም።

89. Posthumous Award of Medals

1/ The appropriate medal shall be registered in the name of a police officer who dies after having accomplished a deed which qualifies for the award of a medal in accordance with this Regulation.

2/ The medal shall be given to his spouse; in default of a spouse, to his eldest descendant; in default of descendant to his heir under the relevant law of succession.

3/ A posthumous promotion of rank may as well be registered in the name of a sacrificed police officer in whose name a Medal of Heroism is registered pursuant to sub-article (1) of this Article.

## PART TWELVE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

90. Grievance Handling Procedure

The Commission shall establish grievance handling procedure to properly address complaints of police officers.

91. Physical Exercise and Sport Competition

The Commission shall create conditions to enable police officers to participate in physical exercises and sport competitions.

92. Relationship with Public

Any police officer shall have the duty to:

1/ in his relations with the public, respect the tradition, culture, beliefs and identity of the community; and

2/ in attending public holidays, wear his uniform and maintain law and order.

93. Prohibition

No police officer may:

1/ participate in a strike;

2/ conduct or participate in a demonstration;

3/ be a member or supporter of any political organization or oppose any political organization;

4/ conduct political agitation openly or covertly;

5/ agitate for or against any political organization or person campaigning for election, or carry or use in any place the emblem of any political organization or any sign it uses for election campaign.

**፺፬. በምርጫ ስለመሳተፍ**

፩/ ማንኛውም የፖሊስ አባል በመንግሥት በሚካሄዱ ምርጫዎች የመምረጥ መብት ይኖረዋል፤ ሆኖም በምርጫ ውድድር ለመሳተፍ የሚፈልግ ከሆነ አግባብ ያላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በቅድሚያ ሥራውን መልቀቅ አለበት፡፡

፪/ በምርጫ ውድድር ለመሳተፍ ሥራውን የለቀቀ የፖሊስ አባል በምርጫው ቢያሸንፍም ቢሸነፍም ተመልሶ በፖሊስ አባልነት ሊቀጠር አይችልም፡፡

**፺፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ኮሚሽኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፺፮. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፺፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም የአሰራር ልማዶች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፺፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፲ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**94. Participation in Election**

1/ Any police officer shall have the right to vote in any election conducted by government; provided, however, that if he intends to compete for election, he has to resign from his position subject to the relevant provisions of this Regulation.

2/ A police officer who has resigned from his position to compete for election may not be re-employed as a police officer irrespective of winning or losing the election.

**95. Power to Issue Directive**

The Commission may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

**96. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The Federal Police Administration Council of Ministers Regulation No. 86/2003 is hereby repealed.

2/ No regulations, directives or customary practices, in so far as they are inconsistent with this Regulation, shall be applicable in respect of matters covered by this Regulation.

**97. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 19th day of November, 2012.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OFETHIOPIA**

## አባሪ

## የማዕረግ እድገት ቆይታ ጊዜ

| የ ማዕረግ ዕርከኖች | የፖሊስ ማዕረግ | የቆይታ ጊዜ (በዓመት) |
|---|---|---|
| የጀማሪ ማዕረግ እርከን | ኮንስታብል | ፫ |
| | ረዳት ሣጅን | ፪ |
| | ምክትል ሣጅን | ፪ |
| | ሣጅን | ፪ |
| | ዋና ሣጅን | ፪ |
| የመካከለኛ ማዕረግ እርከን | ረዳት ኢንስፔክተር | ፪ |
| | ምክትል ኢንስፔክተር | ፫ |
| | ኢንስፔክተር | ፫ |
| የከፍተኛ ማዕረግ እርከን | ዋና ኢንስፔክተር | ፫ |
| | ምክትል ኮማንደር | ፫ |
| | ኮማንደር | ፬ |
| | ረዳት ኮሚሽነር | ፬ |
| | ምክትል ኮሚሽነር | ፬ |
| የስትራቴጂክ ማዕረግ እርከን | ኮሚሽነር | - |
| | ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል | - |
| | ኮሚሽነር ጀነራል | - |

## ANNEX

## PERIOD OF STAY FOR PROMOTION IN RANK

| Levels of Ranks | Police Rank | Period of Stay (Years) |
|---|---|---|
| Junior Level Rank | Constable | 3 |
| | Assistant Sergeant | 2 |
| | Deputy Sergeant | 2 |
| | Sergeant | 2 |
| | Chief Sergeant | 2 |
| Middle Level Rank | Assistant Inspector | 2 |
| | Deputy Inspector | 3 |
| | Inspector | 3 |
| Higher Level Rank | Chief Inspector | 3 |
| | Deputy Commander | 3 |
| | Commander | 4 |
| | Assistant Commissioner | 4 |
| | Deputy Commissioner | 4 |
| Strategic Level Rank | Commissioner | - |
| | Deputy Commissioner General | - |
| | Commissioner General | - |

## አባሪ

## የማዕረግ እድገት ቆይታ ጊዜ

| የ ማዕረግ ዕርከኖች | የፖሊስ ማዕረግ | የቆይታ ጊዜ (በዓመት) |
|---|---|---|
| የጀማሪ ማዕረግ እርከን | ኮንስታብል | ፫ |
| | ረዳት ሣጅን | ፪ |
| | ምክትል ሣጅን | ፪ |
| | ሣጅን | ፪ |
| | ዋና ሣጅን | ፪ |
| የመካከለኛ ማዕረግ እርከን | ረዳት ኢንስፔክተር | ፪ |
| | ምክትል ኢንስፔክተር | ፫ |
| | ኢንስፔክተር | ፫ |
| የከፍተኛ ማዕረግ እርከን | ዋና ኢንስፔክተር | ፫ |
| | ምክትል ኮማንደር | ፫ |
| | ኮማንደር | ፬ |
| | ረዳት ኮሚሽነር | ፬ |
| | ምክትል ኮሚሽነር | ፬ |
| የስትራቴጂክ ማዕረግ እርከን | ኮሚሽነር | - |
| | ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል | - |
| | ኮሚሽነር ጀነራል | - |

## ANNEX

## PERIOD OF STAY FOR PROMOTION IN RANK

| Levels of Ranks | Police Rank | Period of Stay (Years) |
|---|---|---|
| Junior Level Rank | Constable | 3 |
| | Assistant Sergeant | 2 |
| | Deputy Sergeant | 2 |
| | Sergeant | 2 |
| | Chief Sergeant | 2 |
| Middle Level Rank | Assistant Inspector | 2 |
| | Deputy Inspector | 3 |
| | Inspector | 3 |
| Higher Level Rank | Chief Inspector | 3 |
| | Deputy Commander | 3 |
| | Commander | 4 |
| | Assistant Commissioner | 4 |
| | Deputy Commissioner | 4 |
| Strategic Level Rank | Commissioner | - |
| | Deputy Commissioner General | - |
| | Commissioner General | - |